በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛ ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. የዩኒቨርስቲው የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የመደበኛ በጀት ብር 8,064.57 ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣
2. በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በ z ባንክ ሂሳብ ብር 14,495,060.20 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት ሂሳቡ የሚታይ መሆኑ፣
3. የዩኒቨርሲቲው የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የውስጥ ገቢ ሂሳብ የሂሳብ ምዝገባ ያልተደረገ እና ሪፖርትም ያልቀረበ በመሆኑ ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉን፣

4. በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ ከመማር ማስተማር የውስጥ ገቢ ብር 23,569,278.62 የተሰበሰበ ቢሆንም፣
   - በዩኒቨርሲቲው ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የዲፓርትመንቱ ስም እና የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት የክሬዲት ብዛት፣ የትምህርት ዘመን እና ክፍለ ጊዜው (ሴሚስተር) በገቢ ደረሰኙ የማይጠቀስ መሆኑ፣
   - ብዛት ያላቸው ከፋዮች በባንክ ገቢ ያደረጉት ገንዘብ በጥቅል በአንድ ነጠላ የገቢ ደረሰኝ ወይም ቅጠል የሚዘጋጅለት ቢሆንም ከላይ የተጠቀሱትን ተፈላጊ መረጃዎችን የሚገልጹ አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች አባሪ በማድረግ ከገቢ ደረሰኝ ቅጠል ጋር የማይያዙ መሆኑ፣
   - ለዩኒቨርቲው ሥራ አመራርና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፣
5. በውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ መሰረት ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ /ሠራተኛ እና ተማሪ/ ግልጋሎት የተቋቋሙ መዝናኛዎች /ካፌቴሪያ፣ ስፖርት ማዘውተሪያዎች፣ ሬስቶራንቶች ወዘተ/ የሚገኝ ገቢ የውስጥ ገቢ እንደሆኑ የሚገልጽ ቢሆንም ከዩኒቨርሲቲው መደበኛ ገቢ ጋር በመቀላቀል ብር 67,200.00 በገቢ ተይዞ የተገኘ መሆኑ፣
6. በዩኒቨርስቲው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ቁጥር 567001-567050 ድረስ ብር 909,742.78 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ከተደረገዉ ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ፣
7. በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዱራሜ ካምፓስ በድምሩ ብር 111,991.80 ግዥው በየትኛው የግዥ ዘዴ ተወዳድሮ እንደተመረጠ የሚገልጽ ሰነድ ሳይኖርና ለውድድር መቅረብ ሲገባው ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፣
8. ከሰው ኃይል በተገኘ መረጃ መሰረት የተለያዩ ባለሙያዎች ሥራ ከለቀቁ በኋላ ክፍያ በመፈጸሙ የህዳርና የታህሳስ/2009 ብር 5,300.00 ያለአግባብ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
9. ዩኒቨርሲቲው በፐሳ 9 እና ከዚያ በታች ለሆኑ የተፈቀዱ የሥራ መደቦች ሳይኖሩ የአካዳሚክ ባለሙያዎችን በመመደብና ለአካዳሚክ ዳይሬክተሮችና አስተባባሪዎች የተፈቀደውን የኃላፊነት አበል እና አኑዋላይዜሽን ለሥራ መደቡ ያልተፈቀደውን እንዲከፈሉ በመደረጉ ከሥራ ግብር በፊት ብር 1,012,005.22 ከመመሪያ ውጭ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣

10. ዩኒቨርሲቲው በክረምት ወቅት በትርፍ ጊዜያቸው ላስተመሩበት በክሬዲት ሀወር መሰረት መክፈል ሲገባው ሙሉ ደመወዛቸው እንዲሰጥ በመደረጉ ብር 2,457,091.00 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
11. የሚመለከተው ኃላፊ ባንኩ አስፈርሞና ክብ ማህተም በማድረግ የሚላከው ማስረጃ ሳይቀርብና ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሳይሟሉ ብር 5,807,562.59 የደመወዝ ክፍያ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣
12. በ19/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 154243 እና በ16/08/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 590834 ባለሙያዎቹ ከሰሩበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ በላይ ያልተጣራ ብር 10,435.75 የተጣራ ብር 8,346.60 ያለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱን፣
13. አትክልተኞች እና የከብት እርባታ ላይ ለሚሰሩ የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ በቋሚ ቅጥር መሸፈን የሚገባቸው ቢሆንም በተደጋጋሚ በየወሩ በቀን ሰራተኞች ምንዳ /6114/ በሚል ብር 210,580.00 የተከፈለ መሆኑ፣
14. በዩኒቨርሲቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተለያዩ ኮርሶችን ለሚሰጡ ዶክተሮች ውል በመግባት ለእያንዳንዳቸውe በወር ብር 40,000.00 በድምሩ ብር 428,100.00 ለተከፈላቸው ያስተማሩት የክሬዲት ሀወር መጠኑ ባለመገለጹ በውሉ መሠረት ስለመፈጸሙ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
15. በአገር ውስጥ የትምህርት ዕድል ለተሰጣቸው መምህራን መከፈል ከሚገባው በላይ በድምሩ ብር 22,500.00 ከመመሪያ ውጭ ተከፍሎ መገኘቱን፣
16. የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች የመደበኛ ተማሪዎች አካዳሚክ የቀን ጊዜ (ካላንደር) 16 ሳምንት መሆኑ እየታወቀ፣ የ18 ሳምንት ክፍያ (Over Load) እንዲከፈላቸው መደረጉና የትርፍ ሰዓት ክፍያው ከደመወዝ ጋር ሳይደመር የሥራ ግብር በመታሰቡ አለአግባብ ከሥራ ግብር በኂላ (የተጣራ) ብር 477,669.28 የተከፈለ መሆኑ፣
17. የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች የተከታታይ ትምህርት የትርፍ ሰዓት ክፍያው ከደመወዝ ጋር ሳይደመር የሥራ ግብር በመታሰቡ አለአግባብ ከሥራ ግብር በኂላ ብር 648,661.80 የተከፈለ መሆኑ፣
18. በመስክ ላልነበሩ ሰራተኞች ለውሎ አበል ብር 84,591.30 እና ለትራንስፖርት ብር 3,220.00 በድምሩ ብር 87,812.30 ያለአግባብ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

19. የሂሳብ ማወራረጃ ቅፅ 2 ሠራተኛው ለጉዞ የተነሳበት እና የደረሰበት ሰዓትና ቀን እንዲሁም ለሥራ የቆየባቸው ቦታዎች ሳይሞሉ በተሰብሳቢ የተያዘውን የገንዘብ መጠን ብቻ በመውሰድ በድምሩ ብር 209,279.00 በዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ እና የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተወራረደ ቢሆንም የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
20. የመንግስት ሰራተኞች ውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ 2 በተሞላው መሰረት ተመላሽ መደረግ ሲገባው፣ በዱራሜ ካምፓስ ያለ አግባብ ብር 3,640.55 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
21. በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ ለዱራሜ ካምፓስ እና ለጤና ሳይንስ ኮለጅ አስተባባሪ የጸደቀ /የተፈቀደ/ የበላይ ኃላፊዎች /ተሿሚዎች/ የሥራ መደብ ሳይኖር፣ በበላይ ኃላፊዎች የቀን ውሎ አበል መሰረት እየተከፈላቸው በመሆኑ ያለአግባብ ብር 36,638.00 ተከፍሎ መገኘቱን፣
22. ከደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን እና ከከምባታ ጠምባሮ ዞን ም/ቤት ለመጡ በሚል ከዱራሜ ሀዋሳ ሄደው ለሠሩበት በደንቡ መሠረት በዱራሜ የቀን ውሎ አበል ብር 171.00 መሆን ሲገባው፣ በሀዋሳ ብር 202.00 በመሰላቱ ያለአግባብ በድምሩ ብር 11,394.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
23. ብር 33,986.20 ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ (ዊዝሆልዲንግ ታክስ) ከአቅራቢዎች ላይ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
24. ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢ ድረጅቶች ግዥ ሲፈጽም ከተከፋይ ሂሳብ ለተቀነሰ ገንዘብ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ ብር 170,604.15 ደረሰኝ ሳይቆርጥ የተገኘ መሆኑ፣
25. የዩኒቨርስቲው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከአቅራቢዎች ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ (ዊዝሆልዲንግ ታክስ) ብር 47,926.57 እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 216,145.83 በድምሩ ብር 264,072.40 የሰበሰበውን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሳያስተላልፍ በሪፖርት ተመዝገቦ የተገኘ መሆኑ፣
26. ዩኒቨርሲቲው ብር 29,754.00 ከውስጥ ገቢ መክፈል የሚገባውን ከመደበኛ በጀት ለተከታታይ ትምህርት ክፍያ ተፈፅሞ የተገኘ መሆኑ፣
27. በዋናው ግቢ ብር 3,405,421.00 እና በዱራሜ ካምፓስ ብር 36,911.00 በድምሩ ብር 3,442,332.00 ወጪዎች በተገቢው የሂሳብ መደባቸው ሳይመዘገቡ የተገኙ መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ (6218) ቢመዘገብ ኖሮ ለመደቡ ከተደለደለው በጀት በብር 2,881,161.95 ከበጀት በላይ መጠቀማቸውን ያረጋገጠ መሆኑ፣

28. የህንጻ ግንባታ ፍቃድ ባለው በአማካሪ መሐንዲስ መረጋገጥ ሲገባው፣ በተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት መሀንዲስ እና በህ/ሥ/ተቋራጮች በተዘጋጀ የክፍያ ሰርተፊኬት እና በሥራ አመራሩ ፀድቆ ብር 90,157,493.3 እንዲከፈል የተደረገ መሆኑ፣
29. ብር 6,356,593.80 በዋና ግቢ ክፍያው በማስረጃነት መቅረብ የሚገባው የሽያጭ ደረሰኝ /Cash sale invoice/ መሆን ሲገባው፣ የዱቤ የሽይጭ ደረሰኝ /Credit sale invoice/ እንዲቀርብ በማድረግ ሂሳቡ እንዲወራረድ የተደረገ መሆኑ፣
30. የመብራት፣ የውሀ፣ የቴሌኮም እንዲሁም ለተለያዩ ወጪዎች ብር 4,386,682.10 ሲከፈል የወጪ ደረሰኝ በማስረጃነት ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
31. የክፍያው (የወጪው) ማስረጃ ተከታታይ ቁጥር እና የድርጅቱ ስምና አድራሻ አብሮ የታተመ ትክክለኛ
32. ፋክቱር/ደረሰኝ/ ሳይኖረው ብር 60,817.71 በዩኒቨርሲቲ ዱራሜ ካምፓስ ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
33. በዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በወጪ ለተያዘ ሂሳብ ማስተካከያ (Adjustment) በሚል ብር 96,728,320.73 በሂሳብ መዝገብ ተመዝግቦ የተያዘው የማስተካከያ ሂሳብ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ (JV) ከማለት በስተቀር ማስተካከያ የተሰራለትን የወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ ቁጥር፣ ቀንና የገንዘብ ልክ በመጥቀስ ማጣቀሻ ሳይኖር ማስተካከያ የተሰራለትን ወጪ እና የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 38,938,099.53 የወጪ ሂሳብ ሰነዶች በድምሩ ብር 135,666,420.26 ለኦዲት ያልቀረቡ መሆኑ፣
34. ብር 747,592.12 በሂሳብ መዝገብ (TR) ሁለት ጊዜ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
35. ተሰብሳቢ ሂሳብ በድምሩ ብር 173,651,200.77 እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ መወራረድ ሲገባው፣
    - በሂሳብ መደብ 4201 /ልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ/ ብር 859,952.54 ከ1 ወር- 3 ዓመት ለውሎ አበል ቅድሚያ የተከፈለ፣
    - በሂሳብ መደብ 4202 ብር 16,687.39 የጥሬ ገንዘብ ጉድላትተ ለ3 ዓመት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

- በሂሳብ መደብ 4211 ብር 427,525.00 በተለለያዩ ጊዜ ለግዥ ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ ከ 1 ወር-1 ዓመት ያልተወራረደ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4253 /የዕቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ/ የሂሳብ መደብ የሚታየው ብር 170,557,299.54 ከ1 ወር- 3 ዓመት ያልተወራረደ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4274 /ለሌሎች ቅድሚያ ክፍያ/ የሚታየው ብር 1,789,736.30 ከ1 ወር- 5 ዓመት ያልተወራረደ መሆኑ፣

36. በመክፍቻ ሂሳብ/Opening balance/ በተሰብሳቢ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋት/ ሌጀሮች/ ብር 85,385,942.96 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን ክሬዲት ሂሳቡ የሚታይ መሆኑ፣
37. ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 176,421.92 እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ መከፈል ሲገባው ሳይከፈል የተገኘ መሆኑ፣
38. ብር 89,084.00 በግንባታ ምክንያት ከይዞታ ለሚነሱ አረሶ አደር የተፈቀደ በጀት ሳይኖር በ6416 የሂሳብ መደብ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር ከ1 እስከ **36** በተገለጹት ጉልህና በሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>

<u>በጀት፣</u>

- ለመደበኛ(1800) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 14,698,892.48 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- ከዉስጥ ገቢ(1900) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 411,843.00 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው ወጪ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 104,492,885.73 04 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

<u>ንብረት፣</u>

- ብዛት ያላቸው አገልግሎት የማይሰጡ የውሀ ማጠራቀሚያ /ሮቶ/ በቤት ውስጥና ውጭ ላይ ተጠራቅመው የሚገኙ መሆኑ፣
- በተማሪዎች ምግብ ቤት አካባቢ የፍሳሽ ማስወገጃ የተበላሸ በመሆኑ ፍሳሽ በስርዓት የማይወገድ በመሆኑ በሰራተኞችና በተማሪዎች ጤና ላይ ችግር ሊፍጥር የሚችል መሆኑ፣

<u>ልዩ ልዩ፣</u>

- ዩኒቨርሲቲዉን በተመለከተ የስጋት ምንጮች ዳሰሳ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ከተፈቀደለት 1299 የሥራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 638 ሲሆን 661 (51%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፣

<u>የ2008 ኦዲት ሪፖርት እርምጃ ያልተወሰደበት፣</u>

- በዝርዝር ሂሳብ መመዝገቢያ(TR) መሠረት ተመዝግቦ የተገኘው ብር 21,500,537.27 ሲሆን፣ በሂሳብ ቋት የተመዘገበው ደግሞ ብር 14,377,771.31 በመሆኑ በልዩነት ብር 7,122,765.96 የሚታይ መሆኑን፣ ዓመታዊ ሪፖርት የማይዘጋጅና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት የማይደረግ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- ለ14 ሠራተኞች ከብር 1,500-20,000.00 በሥራ አመራሩ ውሳኔ የማበረታቻ ሽልማት ለቢ.ኤስ.ሲ ዕቅድ የሠሩ በሚል ብር 68,000.00 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- ዩኒቨርስቲው ሠራተኞች ሥራ ላይ ስለመሆናቸው ሳያረጋግጥ በድምሩ ብር 42,945.08 ሰራተኞቹ ዩኒቨርሲቲውን ከለቀቁ በኋላ ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር ደመወዝ በሰራተኞች የግል የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑን፤
- ዩኒቨርሲቲው ለለማ ኢንተርናሽናል ሆቴል ብር 40,026.55 መክፈል ሲገባው፣ ብር 10,213.53 በብልጫ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱ፤

- ብር 52,250.38 የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ብር 8,111.77 የተቀናሽ ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 60,362.15 ከአቅራቢው ሳይቀነስ በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱና ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፤**

1.1.1 **ግኝት፤ ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ፤**

በፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል 6 አንቀጽ 7 ተራ ቁጥር 1 እና 2 መሠረት ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ፈሰስ የሚያደርገውን ሂሳብ ተከታትሎ የማስፈጸም፣ የሚፈለግበትን የፈሰስ ሂሳብ መዝግቦ በመያዝ ሂሳቡ ገቢ ተደርጎ መጠናቀቁን ለሚኒስቴሩ ከሐምሌ 30 በፊት ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት ተገልጿል:: ይሁን እንጂ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ብር 8,064.57 ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.1.2 **ስጋት፤**

- ፈሰስ መደረግ የሚገባው ሂሳብ በወቅቱ ፈሰስ ባለመደረጉ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡
- ገንዘቡ ፈሰስ ባለመደረጉ ለሌሎች መ/ቤቶች ሥራ ሊውል የሚችል በጀት አለአግባብ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

1.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

በባንክ የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ እንዲደረግ እና በፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት እንዲገለፅ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ፈሰስ መደረግ የሚገባው ገንዘብ ፈሰስ እንዲደረግ ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይገባዋል፡፡

1.1.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፤**

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ብር 8,064.57 ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገበት ምክንያት ቀደም ሲል ሆስፒታሉ በክልሉ ስር የዞኑ ፋይናንስ አሰራር መሰረት ሆስፒታሉ ያልተጠቀመውን ቀሪ ጥሬ ገንዘብ ሰኔ 30 ላይ በጀት ሲዘጋ የሚወስዱትን ልምድ በማሰብ የዩኒቨርስቲው ፋይናንስ እንደሚወሰድ ታሳቢ በማድረግ የተዘናጋን መሆኑን እየገለፅን፤ ለቀጣይ በጀት ዓመት የባንክ ገቢ ደረሰኝ (RV) የሚቆረጥ እና ያለፈውን ወይም የተገለፀውንም ገንዘብ በ2010 በጀት ተመዝግቦ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑን እንገልፃለን ብለዋል፡፡

1.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በስራ አመራር ምላሹ ላይ የባንክ ሂሳብ ሰኔ 30/2009 ፈሰስ ያልተደረገ ብር 8,064.57 ለነበረው የባንክ ገቢ ደረሰኝ (RV) የሚቀረጥ እና ያለፈውን ወይም የተገለፀውንም ገንዘብ በ2010 በጀት ተመዝግቦ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑ የተገለፀው ሂሳቡ የባንክ ገቢ ደረሰኝ (RV) የሚቆረጥለት ሳይሆን፣ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረግ ሂሳብ መሆኑ ታውቆ ይኸው ሁኔታ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.2.1 ግኝት፣ ሚዛኑን ያልጠበቀ የባንክ ሂሳብ፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/6 ፊደል መ መሠረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጊዜያዊ ሂሳቦች መዝጊያ ምዝገባ ተከናውኖ የዘመኑን ሂሳብ በመዝጋት ቋሚ ሂሳቦች ለቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፍ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበሩ ቋሚ ሂሳቦች በትክክለኛው የሂሳብ ሚዛን /Normal balance side/ ወደ ቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፋቸው ኦዲት ሲደረግ፣

- በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በ z ባንክ ሂሳብ ብር 14,495,060.2 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት ሂሳቡ የሚታይ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

1.2.2 ስጋት፣

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውንና ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ካልተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርቶች የተቋሙን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በትክክል ላያሳዩ ይችላሉ፡፡

1.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይደረግ ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለሂሳቡ ተገቢውን ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

1.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በ IBEX system ምክንያት የተፈጠረ ችግር ስለሆነ በአሁኑ ሰዓት ከ IBEX ሞያተኛ እያመጣን ስለሆነ ችግሩ የሚቀረፍ መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

2. የገቢ ሂሳብ፣

2.1.1 ግኝት፣ ያልተመዘገበ የውስጥ ገቢ ሂሳብ፣

የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 970/2008 እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 62፤,65፤,66 እና 69 መሠረት መንግስት የተቋሙን የገቢና የወጪ ሂሣብን ጨምሮ አግባብነት ያለው የሂሣብ አያያዝና ሪፖርት የማቅረቢያ ሥርዓት መዘርጋት እና ለሁሉም የገቢና የወጪ ሂሣቦች ሥርዓት ያለው የሂሣብ አያያዝ መከተል እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከውስጥ ገቢ ማስገኛ ምንጮች የሚያገኘውን ገቢ በአግባቡ መዝግቦ መያዙን እና የሚከፈሉ ክፍያዎችም በመመሪያ የተደገፉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የውስጥ ገቢ ሂሳብ የሂሳብ ምዝገባ ያልተከናወነ እና ሪፖርትም ያልተደረገ በመሆኑ ኦዲት ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

2.1.2 ስጋት፣

- የተቋሙ የ2009 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫዎች ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበውን ሂሳብ እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ሂሳብ በስራ ላይ የዋለውን ወጪ ያላካተቱ በመሆኑ የሂሳብ መግለጫዎቹ የተቋሙን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በትክክል ሊያሳዩ አይችሉም፡፡
- ከውስጥ ገቢ መሰብሰብ ያለበት ገንዘብ በትክክል መሰብሰቡን እና ወጪ መደረጉን ለማረጋገጥ የማያስችል ከመሆኑም በተጨማሪ የገንዘብ ብክነት ሊከሰት ይችላል፡፡

2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የውስጥ ገቢ ሂሳብ ተገቢና አግባብነት ያለው የሂሣብ አያያዝና ሪፖርት የማቅረቢያ ሥርዓት እንዲዘረጋለት እንዲሁም የፋይናንስ እንቅስቃሴውን የሚገልጹ ወርሃዊ ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫዎች እንዲዘጋጁ ሂሳቡም በየበጀት ዓመቱ እየተዘጋ ኦዲት እንዲደረግ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

2.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ያልተመዘገበ የውስጥ ገቢን በተመለከተ፣

- ዩኒቨርስቲው ሆስፒታሉን ተረክቦ ያስጀመረው ከሐምሌ 1/2008 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ይህ በርክክብ ሂደቱ የቆየ መሆን፣

- በወቅቱ የፋይናንስ ክፍል አዳዲስ ሰዎች የነበሩትና የአሰራር አካሄዱን ባለመገንዘብ፣
- የሃላፊዎች መቀያየርና በወቅቱ ባለመመዝገቡና ባለመታወቁ ወደ ውስጥ ገቢ አካውንት ማስገባት ብቻ ሆኖ የቆየ ስለነበረ በመሆኑም ይህ ዓይነት ችግር በድጋሚ እንዳይፈጠር የ2010 በጀት ዓመቱን በሚፈቀዱ ኮዶች ላይ በመሸንሸን እና የጤና አገልግሎት ጥራቱን ለማሻሻል በመመሪያው መሰረት ወደ ስራ የተገባ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- የውስጥ ገቢ በበጀት ዓመቱ ያልጸደቀ በመሆኑ በ IBEX ተመዝግቦ ሪፖርት ለማድረግ የማይቻል ስለሆነ የ IBEX ምዝገባ አልተከናወነም፡፡ በሚቀጥለዉ ጊዜ በጀት ታውጆ ከጸደቀ የሚመዘገብ መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

2.2.1 ግኝት፣ የገቢው ዓይነት ያልተገጸ የውስጥ ገቢ፣

በፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት የገቢ መቀበያ ደረሰኝ ተፈላጊውን መረጃ አሟልቶ መያዝ እንዳለበት የተደነገገ እና በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 970/2008 እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/200 አንቀጽ 62፣ 65፣ 66 እና 69 መሠረት የመንግሥት ተቋም የገቢና የወጪ ሂሳብን ጨምሮ አግባብነት ያለው የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት የማቅረቢያ ስርዓት መዘርጋትና ለሁሉም የገቢና ወጪ ሂሳቦች ስርዓት ያለው የሂሳብ አያያዝ መከተል እንደሚገባ በአዋጁ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ከመማር ማስተማር ገቢዎች የውስጥ ገቢ ብር **23,569,278.62** የተሰበሰበ ቢሆንም፣

- በዩኒቨርሲቲው ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የዲፓርትመንቱ ስም እና የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፣ የክሬዲት ብዛት፣ የትምህርት ዘመን እና ክፍለ ጊዜው በገቢ ደረሰኙ የማይጠቀስ መሆኑ፣
- ብዛት ያላቸው ከፋዮች ባንክ ገቢ ያደረጉት ገንዘብ በጥቅል በአንድ ነጠላ የገቢ ደረሰኝ ወይም ቅጠል የሚዘጋጅ በመሆኑ ተፈላጊ መረጃዎችን የሚገልጹ አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች አባሪ በማድረግ ከገቢ ደረሰኝ ቅጠል ጋር የማይያዙ መሆኑ፣
- የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት ለዩኒቨርስቲው ሥራ አመራርና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ያልቀረበ መሆኑ፣

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.2.2 ስጋት፣

የገቢ ደረሰኝ ተፈላጊውን መረጃ አሟልቶ ካልያዘ ወይም አግባብነ ባላቸው ሰነዶች ካልተደገፈ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥም ሆነ የተሟላ አስተያየት ለመስጠት አያስችልም፡፡

2.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- የሂሳብ ሪፖርቶች የተቋሙን የፋይናንስና የስራ እንቅስቃሴ በትክክል እንዲገልጹ ከተለያዩ ገቢ ማስገኛ ምንጮች የሚገኘው ገቢ በሙሉ ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡
- የገቢ ደረሰኝ ተፈላጊውን መረጃ አሟልቶ እንዲይዝ ወይም አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች አባሪ በማድረግ ከገቢ ደረሰኝ ቅጠል ጋር እንዲያያዙ፤ እንዲሁም የሚሰበሰቡትን ገቢዎች በሙሉ ሪፖርት ውስጥ በማካተት ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ በማድረግ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

2.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በሚመጣዉ ደረሰኝ ላይ የሚጠየቀዉ ክፍት ቦታ በሙሉ የተሞላ ሲሆን ከላይ እንደ አስተያየት የቀረበውን የሚካተቱ ነገሮችን በተቻለ መጠን ክፍት ቦታዎች ባይኖሩም ለመጨመር እንሞክራለን፡፡ ሪፖርትም ኦዲተር ኦዲት ካደረገ በኋላ ለሚመለከተዉ ክፍል ሪፖርት እናደርጋለን ብለዋል፡፡

2.3.1 ግኝት፣ የውስጥ ገቢን ከመደበኛ በጀት ጋር በመቀላቀል ተይዞ መገኘቱ፣

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 ውስጥ ከተዘረዘሩት አንዱ ለዩንቨርሲቲው ማህበረሰብ /ሠራተኛ እና ተማሪ/ ግልጋሎት ለመስጠት የተቋቋሙ መዝናኛዎች /ካፍቴሪያ፣ ስፖርት ማዘውተሪያዎች፣ ሬስቶራንቶች ወዘተ/ የሚገኝ ገቢ የውስጥ ገቢ እንደሆነ የሚገልጽ ቢሆንም፣ ከዩኒቨርሲቲው መደበኛ ገቢ ጋር በመቀላቀል ብር 67,200.00 በገቢ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

2.3.2 ስጋት፣

የመደበኛ በጀት እና የዉስጥ ገቢን ትክክለኛነት ላያሳይ ይችላል፡፡

2.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በውስጥ ገቢ አርዕስቶች የተሰበሰበው የገቢ ሂሳብ ወደ ውስጥ ገቢ ተመላሽ ለማድረግ በ1489 በመደበኛ ገቢ ሂሳብ መደብ የተያዘውን ወደ 1444 የውስጥ ገቢ ሂሳብ መደብ መቀየር ይገባል፡፡

2.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በገቢ ሂሳብ መደብ 1489 ልዩ ልዩ ገቢ የሚባሉ ከመደበኛ ተማሪዎች የምዝገባ፣ ቅጣት፣ የመታወቂያ ካርድ፣ የጨረታ ማስከበሪያ፣ cpo ሲወረስ እና ከመደበኛ በጀት ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ገቢዎች የሚመዘገብበት ቢሆንም ለወደፊት ከመዝናኛ ካፍቴሪያዎች ኪራይና ከትምህረታዊ ተቋማት ገቢ ጋር በገቢ ሂሳብ መደብ 1444 ላይ መመዝገብ የሚቻል መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

2.4.1 ግኝት፣ ሪፖርት ከተደረገዉ ውስጥ ያልተካተተ የውስጥ ገቢ ሂሳብ፣

በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 970/2008 እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/200 አንቀጽ 62፣ 65፣ 66 እና 69 መሠረት የመንግሥት ተቋም የገቢና የወጪ ሂሳብን ጨምሮ አግባብነት ያለው የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት የማቅረቢያ ስርዓት መዘርጋትና ለሁሉም የገቢና ወጪ ሂሳቦች ስርዓት ያለው የሂሳብ አያያዝ መከተል እንደሚገባ በአዋጁ የታዘዘ ቢሆንም፣ ዩኒቨርስቲው ከልዩ ልዩ ምንጮች የሚሰበስበው የውስጥ ገቢ ኦዲት ሲደረግ፣ በዩኒቨርስቲው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ 567001-567050 ብር 909,742.78 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

2.4.2 ስጋት፤

- ዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ የሚያዘጋጀው የገቢ ሂሳብ ሪፖርት የዩኒቨርሲቲውን ትክክለኛ የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ እንዳያሳይ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- አገልግሎት በመስጠት የሚሰበሰበው ገቢ በገቢ ሂሳብ መደብ ተገልጾ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ዉስጥ በማጠቃለል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት የሚሆንበት ስርዓት ካልተዘረጋ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- መንግስት ሊያገኝ የሚገባዉን ገቢ ሊያሳጣ ይችላል፡፡

2.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ዩኒቨርሲቲዉ በበጀት ዓመቱ የሰበሰበውን ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የገቢ ሂሳብ ሪፖርት እንዲካተት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

የውስጥ ገቢን በተመለከተ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚ/ር በየወሩ ለመላክ በዓመት ውስጥ የሚጸድቀውና በዓመት ውስጥ የሚሰበሰበው እኩል ስላልሆነ በሪፖርት ውስጥ ለማጠቃለል አልተቻለም፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከIBEX ሞያተኛ አስመጥተን እንዴት መመዝገብ እንዳለብን ሞያዊ እገዛ ስለተደረገልን ለቀጣይ በየዓመቱ በሚል ሪፖርት እንዲዘጋጅ ተደርጓል ብለዋል፡፡

2.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፤</u>

በዩኒቨርስቲው በአንድ ጥራዝ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ከቁጥር 567001-567050 ድረስ ብር 909,742.78 የተሰበሰበው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ እንጂ የ IBEX የአመዘጋገብ ችግር አይደለም፡፡ ስለሆነም የተሰበሰበው ገቢ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት እንዲካተት መደረግ ይኖርበታል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሳብ፤</u>

3.1.1 <u>ግኝት</u>፤ <u>ያለውድድር (ፕሮፎርማ ሳይሰበሰብ) በቀጥታ የተፈፀመ የአገልግሎት ግዥ፤</u>

የካምፓሱን የግዥ ሂደት በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ታህሳስ 1/2008 ዓ.ም ክፍል 9 አንቀጽ 25(7) (ሀ) የመንግስት መ/ቤት በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 5,000.00 ያልበለጠ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር የታያያዙ የቀጥታ ግዥዎችን ከማናቸዉ ሻጭ ድርጅት መፈፀም ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈፀሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ዉስጥ ከብር 75,000 መብለጥ አይኖርበትም የሚል ሲሆን በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዱራሜ ካምፓስ በድምሩ ብር 111,991.80 ግዥው በየትኛው የግዥ ዘዴ ተወዳድሮ እንደተመረጠ የሚገልጽ ሰነድ ሳይኖርና ግዥውም ለውድድር መቅረብ ሲገባው ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	27/07/09	156534	6233	34,593.36
2	20/08/09	156549	6233	19,774.54
3	23/09/09	396503	6233	19,463.90
4	05/10/09	396506	6216	38,160.00
ድምር				111,991.80

3.1.2 ስጋት፣

- በውድድር ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ሊያሣጣ ይችላል፡፡
- በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥ ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት ይህም ቁጠባን ፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዥዎችን ሲፈፀሙ ተገቢውን የመንግስትን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ተከትሎ መሆኑ በማረጋገጥ ክፍያ መፈጸም ይገባል። ግዢ በሚያስፈልግበት ወቅት ጨረታሊወጣ ይገባል እንጂ በ2008 የወጣው ጨረታ ተወዳዳሪ አልነበረውም ስለተባለ ብቻ በ2009 ተደግሞ እዚያው ቦታ የአገልግሎት ግዥው መፈፀሙ አግባብ አይደለም። ይህም በ2009 ተወዳዳዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ጨረታውን በማውጣት የውድድሩን ውጤት ማየት ይገባ ነበር። ስለሆነም ለወደፊት እንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

3.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በ2008 በጀት ዓመት በዋና ግቢ በኩል በወጣው ጨረታ መሰላ ሆቴል እና ቱሪዝም አሸናፊ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዞኑ ውስጥ ሌሎች ተፎካካሪ ሆቴሎች ስለሌሉና አገልግሎቱንም በማኔጅመንት ውሳኔ መሠረት ውሉን በማራዘም የተጠቀምነው አገልግሎት እንጂ በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ አይደለም ብለዋል፡፡

3.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በስራ አመራር ምላሹ ላይ ማስረጃ ተያይዟል የተባለው ለ2010 በጀት ዓመት በ04/12/2009 ከሆቴሉ ጋር የአገልግሎት ስራ ውል የገቡበት እና የውል ማራዘሚያ ቃለ ጉባኤ እንጂ ለ2009 በጀት ዓመት ጨረታ ወጥቶ ብቸኛ ተወዳዳሪ ለመሆኑ ከግዥ ኤጀንሲ የተፈቀደበት ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ለወደፊት ውል ማደስ ብቻ ሳይሆን ብቸኛ ተወዳዳሪ ለመሆኑ ከግዥ ኤጀንሲ የተፈቀደበት ደብዳቤ ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.2.1 ግኝት፣ ያለ አግባብ የተከፈለ ደመወዝ፣

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 12 የመንግስት ሠራተኞች የደሞዝ ክፍያ አፈጻጸም መስረት በንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ሀ፣ለ እና ሐ እንደሚገልፀው ሠራተኛው ከ20ኛው እስከ 30ኛው ቀናት ውስጥ በሥራ ላይ ካልተገኘና በአስተዳደር ተረጋግጦ ተመላሽ እንዲደረግ ሲውስን በሚቀጥለውም ወር በሚዘጋጀው ማረጋገጫ ላይ ተገልጾ ከዚያው ወር ደመወዙ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል ይላል፡፡ ሆኖም ይህን ለማረጋገጥ የደመወዝ አከፋፈል ኦዲት ሲደረግ፣ ከሰው ሀይል በተሰጠው መረጃ መሰረት የተለያዩ ባለሙያዎች ስራ ከለቀቁ በኋላ ክፍያ በመፈጸሙ የህዳርና የታህሳስ/2009 ብር 5,300.00 ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**

ተ.ቁ	የወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር	ስም	የለቀቀበት ቀን	የወር ደመወዝ	ጠቅላላ ተከፋይ	የስራ ግብር	የጡረታ መዋጮ	የተጣራ ተከፋይ
1	289309	መነን ወልደ	01/03/2009	688.00	688	8.8	48.16	631.04
	166236			688.00	688	8.8	48.16	631.04
2	289309	ሙሀባ የሱፍ ኢብራሂም	30/03/2009	1916.00	1,916	144.9	134.12	1,636.98
3	166236	መስከረም ኦላና	30/02/2009	2008.00	2008	158.7	140.56	1708.74
			ድምር	5,300.00	5,300.00	321.20	371.00	4,607.80

3.2.2 ስጋት፣

የመንግስትን ገንዘብ ያለ አግባብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

3.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ያለ አግባብ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊትም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የለቀቁ ሰራተኞችን ክትትል በማድረግ ያለአግባብ የተከፈለውን ገንዘብ እናስመልሳለን ብለዋል፡፡

3.3.1 ግኝት፣አለአግባብ ለአኑዋላይዜሽንና ለኃላፊነት አበል የተከፈለ፣

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬልና ጥቅማ ጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚንስትሮች ምክር ቤት መሆኑ የተደነገገ ሲሆን፣ በተጨማሪም የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ ‹‹ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ መጠን ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከ አሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ መጠን እና ጥቅማ ጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ አሳውቋል፡፡ ይሁን እንጂ በ2009 በጀት ዓመት ዩኒቨርሲቲው በፐሳ 9 እና ከዚያ በታች ለሆኑ የተፈቀደ የስራ መደብ ሳይኖር የአካዳሚክ ባለሙያዎችን በመመደብና ለአካዳሚክ ዳይሬክተሮችና አስተባባሪዎች የተፈቀደውን የኃላፊነት አበል እና አኑዋላይዜሽን ለስራ መደቡ ያልተፈቀደውን እንዲከፈሉ በመደረጉ ብር 1,012,005.22 ያልተጣራ ከመመሪያ ውጭ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

3.3.2 ስጋት፣

- መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡
- የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

- ከህግ እና መመሪያ ዉጭ የሆኑ ዉሳኔዎችን በመወሰን የሚከፈል ክፍያ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድም ሆነ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተለያዩ ውሳኔዎችን ሲወስን መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸውን አዋጆችና መመሪያዎች መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡
- ለስራ መደቡ በተፈቀደው መሰረት ባለሙያዎችን መቅጠር ያስፈልጋል፡፡ በአካዳሚክ ባለሙያዎች እንዲያዝ ከተፈለገም በሚመለከተው አካል መዋቅሩን ማስቀየር ያስፈልጋል፡፡
- በመከፈል ላይ ያሉ ክፍያዎች በመመሪያ ያልተደገፉ በመሆኑ ክፍያው እንዲቆም ተደርጎ እስከ አሁን ያለ አግባብ የተከፈለውም ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- አዲስ መዋቅር በሚያስፈልግበት ጊዜ በቅድሚያ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርን ማስፈቀድ ይገባል፡፡

3.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ከላይ የተገለጽዉ የአስተዳደር ዘርፍ ጊዜያዊ የስራ ውክልና ተሰጥቶ የተገኘበት ምክንያት ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር መ/ቤት በቀን 11/02/2009 በቁጥር ፐ/ሰ/ሚ/ጠ10/86/648 በተፃፈዉ ሰርኩላር ለማንኛዉም የፌደራል ተቋማት እና ከፍተኛ የትም/ት ተቋማት አዲስ እና ደረጃቸው እንዲሻሻል የተጠየቁ መደቦች ሚ/ር መ/ቤቱ እገዳ ያስተላለፈ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲው አመራር የተቋሙን አንገብጋቢ የስራ ሁኔታዎች ላይ ጊዜያዊ የስራ ውክልና ለመስጠት የዩኒቨርሲቲውን መደበኛ ስራ ለማስቀጠል የተወሰደ እርምጃ መሆኑን እየገለጽን ለዚህ አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ እንደ ማሳያ 5/አምስት ገጽ ጊዜያዊ ውክልና የተሰጠበት እና የፐብሊክ ሰርቪስ እገዳ ሰርኩላር 5/አምስት ገጽ አያይዘን አቅርበናል ብለዋል፡፡

3.3.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በስራ አመራር ምላሹ ላይ የዩኒቨርሲቲው አመራር የተቋሙን አንገብጋቢ የስራ ሁኔታዎች ላይ ጊዜያዊ የስራ ውክልና ለመስጠት የዩኒቨርሲቲውን መደበኛ ስራ ለማስቀጠል የተወሰደ እርምጃ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ሆኖም ከመመሪያ ውጭ ተጨማሪ ወጪ የሚያስከትሉትን የአካዳሚክ ባለሙያዎችን የአስተዳደር ስራ ላይ በመመደብ ጊዜያዊ የስራ ውክልና ከመስጠት

ይልቅ ከአስተዳደር ሰራተኞች ብቃት ያላቸውን በመለየት ጊዜያዊ የስራ ውክልናው ቢሰጥ ከተጨማሪ ወጪ ሊያድን ስለሚችል አሰራሩ በዚሁ ሊስተካከል ይገባል፡፡

3.4.1 ግኝት፣ በክረምት ላስተማሩ መምህራን በድጋሚ የተከፈለ፣

የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ምእራፍ 13 ስለ ትርፍ ሰዓት ስራ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የትርፍ ሰዓት ስራ ለሰራ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በሰራተኛው ምርጫ መሰረት የማካካሻ እረፍት ወይም የትርፍ ሰአት ክፍያ ይሰጠዋል፡፡ በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ሚያዚያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም በቁጥር ት/ሚ.259/82-18/03 የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያን በተመለከተ ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት በሳምንት ከ12 ሰዓት በላይ የሚሰራ ከሆነ ‹‹ለሙሉ፤ ለተጠባባቂ እና ረዳት ፕሮፌሰር 120፤ ለሌክቸር 100፤ ረ/ሌክቸር እና ምሩቅ 65፤ እና ለቴክኒክ ረዳት 45 በዚሁ ተመን ስሌት እንደሚከፈላቸው ተገልጿል፡፡ በዚህም መሰረት ዩኒቨርሲተው በክረምት ወቅት በትርፍ ጊዜያቸው ላስተመሩበት በክሬዲት ሀወር መሰረት መክፈል ሲገባው፣ ሙሉ ደመወዛቸውን ብር 2,457,091.00 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**

ተ.ቁ	ቀን	የሂሳብ መደብ	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የገንዘብ መጠን
1	19/12/08	6116	166207	2,323,584.00
2	03/13/08	6116	166214	68,857.00
3	14/03/09	6116	496137	64,650.00
			ድምር	2,457,091.00

3.4.2 ስጋት፤

- የመንግስት ገንዘብ አለአግባብ ወጭ ሊሆን ይችላል፡፡

- የመደበኛ የትምህርት ፕሮግራምን ክረምት ላይ እንዲደርስ ማድረግ ተጨማሪ ወጭ ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ከመመሪያ ወጭ ክፍያዎችን መፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- የመማር ማስተማሩ ሂደት በመደበኛ የሥራ ወቅት የሚያልቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡
- ከአቅም በላይ በሆነ ችግር የመማር ማስተማሩ ክረምት የሚደርስ መሆኑ ከታወቀ ክረምት ቀርተው ለሚያስተምሩ መምህራን ከመምህራኖች ጋር በመነጋገር ፈቃደኛ ከሆኑና ከመደበኛ የትምህርት መርሀ ግብር ጋር ማጣጣም የሚቻል ከሆነ ሌሎች ወራቶች ላይ የማካካሻ እረፍት መስጠት ይህ ካልተቻለ ግን ለሰሩበት የሥራ ሰአት ብቻ ታስቦ ክፍያ እንዲፈጸም በማድረግ በልዩነት የወሰዱትን ተመላሽ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

3.4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የኒቨርሲቲዉ በ2008 ዓ.ም የተከታታይ ትምህርት ዘመን የ1ኛ ዓመት የሁሉም ኮሌጆች ተማሪዎች ካላንደር ወደ ክረምት በመግባቱ ኮርሶችን ይዘዉ በእረፍት ጊዜያቸዉ (ሀምሌና ነሀሴ ወራት) ሲያስተምሩ ለቆዩ መምህራን የተከፈለ የአንዋላይዜሽን ክፍያ ሲሆን ይህም፡-

1. ግንባታ በመዘግየቱና ዩኒቨርሲቲዉ ከዕቅድ ውጪ የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች መመደባቸዉ፣
2. የህክምናና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ በተለይም የሜዲሲን ተማሪዎች የትምህርት ካላንደር 12 (አስራ ሁለት) ወር መሆኑ፣
3. ሌሎች ከአቅም በላይ በመሆኑ ችግሮች ምክንያት ተማሪዎችን (1ኛ ዓመት) ህዳር መጨረሻ ላይ በመቀበላችን ነዉ፡፡

በ2009 ዓ.ም ከህክምና ሳይንስ ኮሌጀ ተማሪዎች ውጪ የሌሎች ኮሌጅ ተማሪዎች የትምህርት ካሌንደር እስከ ሰኔ 30/10/2009 ዓ.ም ድረስ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህም የማስተካከያ ስራ መሰራቱን ይገልጻል ብለዋል፡፡

3.5.1 ግኝት፣ የደመወዝ አከፋፈል፣ ማስረጃ አቀራረብና ምዝገባን በተመለከተ፣

የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ በባንክ በኩል ለመክፈል የፋይናንስ ተግባርን የሚያከናውነው የሥራ ክፍል ማከናወን ያለበትን ተግባሮች ይዘረዝራል ከዚህ ውስጥ፡-

ነ. ለወሩ ጥቅል የተጣራ የመስሪያ ቤቱን የሰራተኛ ደመወዝ ቼክ በመፈረም እና የሠራተኛውን ስም፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እና የተጣራ የደመወዝ መጠን የያዘ ዝርዝር በሁለት ኮፒ በማዘጋጀት ክፍያ ወደሚፈጽመዉ ባንክ ያስተላልፋል፣

ሸ.ባንኩ በተላለፈለት ዝርዝር መሰረት የሰራተኛዉን የተጣራ ደመወዝ ወደ ሠራተኛው የቁጠባ ሂሳብ ካስተላለፈ በኂላ ከመስሪያ ቤቱ በኮፒ ተዘጋጅቶ የተላከለትን የሰራተኛዉን ስም፣የባንክ ሂሳብ ቁጥርና የሚተላለፈዉን የገንዘብ መጠን የያዘዉ ሰነድ ላይ የሚመለከተዉ ኃላፊ ፈርሞበት ክብ ማህተም በማድረግ አንድ ኮፒ መልሶ እንዲላክለት ያደርጋል፣

ቀ.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሸ) በተገለፀዉ ማስረጃና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና ከኢትዮያ ንግድ ባንክና በሚደርሰዉ የዴቢትና የክሬዲት አድቫይስ መሠረት ለወጪዉ አስፈላጊዉን የሂሳብ ምዝገባ ያከናዉናል፣

ተ. ከባንኮቹ የሚቀርቡትን የዴቢትና የክሬዲት አድቫይሶችና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሸ) የተገለፀዉን ማስረጃ ከደመወዝ መክፈያ ዝርዝር ጋር በማያያዝና በማወራረስ ሂሣቡን ይመዘግባል ያስመረምራል `በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መልኩ እንደሚከናወን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለሰራተኞች የጥቅማ ጥቅም እና ደመወዝ ክፍያ ሲፈጽም የሰራተኛውን የተጣራ ደመወዝ ወደ ሠራተኛው የቁጠባ ሂሳብ እንዲተላለፍ ከተላከ በኂላ የባንክ አድቫይስ እና ከመስሪያ ቤቱ በኮፒ ተዘጋጅቶ የተላከለትን የሰራተኛውን ስም፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥርና የሚተላለፈውን የገንዘብ መጠን የያዘዉ ሰነድ ላይ የሚመለከተዉ ኃላፊ ባንኩ አስፈርሞና ክብ ማህተም በማድረግ የሚላከው ማስረጃ ሳይቀርብና ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሳይሟሉ ክፍያው በወጪ የተመዘገበ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡**ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**

ተ.ቁ	ቀን	የወጭ ማስመስከሪያ	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	27/11/2008	166201	6111	4,676,087.00
			6121	953,859.08

2	05/01/09	166220	6121	3,650.00
3	03/04/2009	166250	6111	23,554.00
4	24/04/2009	289306	6111	48,321.04
			6121	6,483.98
5	27/04/09	289310	6111	87,684.19
			6121	7,923.3
			ድምር	5,807,562.59

3.5.2 ስጋት፤

ከወጪ ማስረጃዉ ጋር የተያያዘዉ ዝርዝር እና ለባንክ የተላከዉ ዝርዝር አንድ ዓይነት መሆኑን መከፈል ባለበት ልክ እና መከፈል ላለበት ሰው መከፈሉን ማረጋገጥ ላያስችል ይችላል፡፡

3.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው የደመወዝ ክፍያ ሲፈጽም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚደርሰዉ ለሰራተኞች እንዲከፈል የተላከበትን ኮፒ እና የዴቢትና የክሬዲት አድቫይስ እየተቀበለ ምዝገባውን ማከናወን አለበት፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ምዝገባዎች ሲከናወኑ ጥብቅ የሆነ ክትትል መደረግ ይገባዋል፡፡

3.5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፤

ደመወዝ ለባንክ የሚላከዉ hard copy እና soft copy ሲሆን ባንኩ ደብዳቤ በሚቀበልበት ሰዓት ከ soft copy ጋር upload ነዉ ወደ እያንዳነዱ ሰራተኞች አካዉንት ገቢ የሚደረገዉ፡፡ Advice የሚሰጠን በአጠቃላይ የገባዉን እንጂ ለእያንዳንዱ አይሰጠንም በአጠቃላይ ለገባዉ Advice አስመጥተን አያይዘናል ብለዋል፡፡

3.5.5 የኦዲተሩ አስተያየት፤

በስራ አመራር ምላሹ ላይ አድቫይስ የሚሰጠን በአጠቃላይ የገባውን እንጂ ለእያንዳንዱ አይሰጠንም በአጠቃላይ ለገባው አድቫይስ አስመጥተን አያይዘናል ለተባለው በግኝቱ ላይም አድቫይስ እንዲቀርብ የተጠየቀው በአጠቃላይ ለገባው እንጂ ለእያንዳንዱ አይደለም፡፡ በተጨማሪም አድቫይስ አስመጥተን አያይዘናል ለተባለው በመውጫ ስብሰባ ወቅት

የተያያዘው አድቫይስ እንዲቀርብ ተጠይቆ የሚቀርብ መሆኑ ተገልፆ ነበር፡፡ ሆኖም ሊቀርብ አልቻለም፡፡ ስለሆነም ለወደፊት በአጠቃላይ ለገባው ሂሳብ የባንክ አድቫይስ እና ከመስሪያ ቤቱ በኮፒ ተዘጋጅቶ የሚላከውን የሰራተኛውን ስም፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥርና የሚተላለፈዉን የገንዘብ መጠን የያዘዉ ሰነድ ላይ የሚመለከተዉን የባንኩን ኃላፊ አስፈርሞና ክብ ማህተም በማስደረግ ከደመወዝ መክፈያ የወጪ ማስመስከሪያ ጋር ተያይዞ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

3.6.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ያለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣</u>

የቀድሞ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 በቀን ሰኔ 29/2001 ዓ.ም ያስተላለፈው የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ መመሪያ እንዲቆም በቁጥር መ30/ጠ13/37/820 በቀን 5/13/2001 ዓ.ም በተጻፈ መመሪያ የገለጸ ቢሆንም፣ ተቋሞች ከአቅም በላይ የሆነ ችግር በሚያጋጥማቸው ወቅት በቅድሚያ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን በማስፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንደሚፈጽሙ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፣ በ19/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 154243 እና በ16/08/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 590834 ባለሙያዎቹ ከሰሩበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ በላይ ያልተጣራ ብር 10,435.75 የተጣራ ብር 8,346.60 ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.6.2 <u>ስጋት፤</u>

የወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና የአፈፃፀም መመሪዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡ መንግሥት ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

3.6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ክፍያ በሚፈጸምበት ጊዜ መንግስት ባወጣው የአከፋፈል መመሪያ መሰረት በትክክል መሰራቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡
- ከባለሙያዎቹ ያለአግባብ የተከፈላቸው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.6.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የዋቸሞ የኒቨርሲቲ የስራ ሁኔታ በመደበኛ የስራ ሰዓት መሸፈን የማይቻል ሆኖ ሲገኝ በደበዳቤ በመጠየቅና በማስፈቀድ የተሰራ መሆኑን እንገልጻለን የሰዓት ክፍያ ስሌት በወር ውስጥ 160 ሰዓት ማለትም በቀን 8 ሰዓት × በሳምንት 5 ቀን × በወር ውስጥ 4 ሳምንት በሚል የተሠራ

ሲሆን ለ240 ሰዓት ስሌት ይሠራ የተባለውን ወይም በተረኝነት አበል ክፍያ ስሌት ይሠራ የተባለው ትክክል ከሆነ ወደ ፊት የምናስተካክል መሆኑን እናሳውቃለን ብለዋል፡፡

3.6.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

- በስራ አመራር ምላሹ ላይ የዋቸሞ የኒቨርሲቲ የስራ ሁኔታ በመደበኛ የስራ ሰዓት መሸፈን የማይቻል ሆኖ ሲገኝ በደበዳቤ በመጠየቅና በማስፈቀድ የተሰራ መሆኑን እንገልጻለን ለሚለው በግኝት የተጠየቀው ባለሙያዎቹ ከሰሩበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ በላይ ያለአግባብ ተከፍሎ ስለመገኘቱ እንጂ ባልተፈቀደ ክፍያ የተከፈለ ስለመሆኑ አይደለም፡፡ ሌላው በወር ውስጥ 160 ሰዓት ማለትም በቀን 8 ሰዓት × በሳምንት 5 ቀን × በወር ውስጥ 4 ሳምንት በሚል የተሠራ መሆኑ ለተገለፀው ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የወር ደመወዝ የሚከፈለው በአንድ ወር ለ30 ቀናት እንጂ 22 የስራ ቀናትን ብቻ ስላልሆነ የተረኝነት አበል ደግሞ የሰዓት ገደብ ሳይኖረው በሰሩበት ሰዓት ልክ የሚከፈል በመሆኑ 60 የስራ ሰዓት ከዚህ ውጭ ለሆኑ ስራዎች የሚከፈል ነው፡፡

  ለማሳያ በአባሪ 11 ከተያዘው ሰንጠረዥ ውስጥ ተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ቢሰራ

  - **በኦዲተሮች ፡- ደመወዝ 2,197/ 240 ሰዓት= 9.1542 * 60 ሰዓት =549.252*2 (ቅዳሜና እሁድ ስለሰሩ) = 1,098.50 ሲሆን**
  - **በዩንቨርስቲው ፋይናንስ ክፍል፡- ደመወዝ 2,197/160 ሰዓት= 13.73125 * 60 ሰዓት =823.875*2 (ቅዳሜና እሁድ ስለሰሩ) = 1,647.75**

    ልዩነት 1647.75-1098.50= 549.25 ከተሰራበት ክፍያ በላይ የተከፈለ

  ስለሆነም ባለሙያዎቹ ከሰሩበት ክፍያ በላይ የተከፈላቸው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.7.1 ግኝት፣ የቀን ሰራተኞች ሂሳብን በተመለከተ፣

ሰብዓዊ ለሆኑ ክፍያዎች በደንብና መመሪያው መሰረት እየተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በተላለፈ መመሪያ ቁጥር ሲሰሚ30/ጠ18/22/459 በቀን 16/04/2005 ዓ.ም ‹‹በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተለመደና ዘላቂነት በሌለው የስራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሰራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ እንዲሰናበቱና ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ቅጥር እንዳይፈጸም››

መመሪያው ቢያመለክትም፣ ዩኒቨርሲቲው በሚያከናውነው የምርምር ስራ ላይ የሚሰሩ አትክልተኞች እና የከብት እርባታ ላይ ለሚሰሩ የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ በቋሚ ቅጥር መሸፈን የሚገባቸው ቢሆንም በተደጋጋሚ በየወሩ በቀን ሰራተኞች ምንዳ /6114/ በሚል ብር 210,580.00 ለኦዲት በተመረጡት የወጭ ማስመስከሪያዎች የተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር	የገንዘብ መጠን	መግለጫ
1	30/10/09	431482	47,700	ሾኔ የምርምር ማዕከል
2	30/10/09	431471	25,200	ለምቡዳ ምርምር ማእከል
3	30/10/09	431468	19,680	ዋና ግቢ ሰብል ልማት
4	30/10/09	431469	14,000	ዋና ግቢ ከብት እርባታ
5	30/10/09	431459	14,000	የከብት እርባታ ሰራተኞች
6	30/10/09	431465	45,000	ሾኔ ምርምር ማእከል
7	30/10/09	431458	19,800	ዋና ግቢ ሰብል ልማት
8	30/10/09	431481	25,200	ሽንቆላ ምርምር ማዕከል
		ድምር	210,580.00	

3.7.2 ስጋት፤

ከመመሪያና ደንብ ውጭ ክፍያዎችን መፈፀም የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የስራ መደቦቹን በማስፈቀድ በቋሚ ቅጥር ማሰራት ይገባል፡፡

3.7.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲቲያችን የተለያዩ የምርምር ማዕከላትና የግብርና ማዕከላትን ማለትም ሸንቆላ፣ ለምቡዳ እና ሾኔ በመረከቡ ምክንያት በማዕከላቶቹ ቋሚ ሠራተኞችንም ጭምር በመረከቡ ሥራውን ለማስቀጠል ሲባል በቀን ሠራተኝነት የተከፈለበት ምክንያት ሲቪል ሰርቪስ አዳዲስ መደቦችን እንዳናስፈቅድ የእገዳ ደብዳቤ ያስተላለፈ በመሆኑ አማራጭ በመጥፋቱ ወሩን ሙሉ የሚሠሩትን ሠራተኞች የቀን ሠራተኛ ምንዳ በሚል ክፍያ ተፈጽሟል ለወደፊቱ ግን ሲቪል ሰርቪስን የምናስፈቅድ ይሆናል በማለት ገልፀዋል፡፡

3.8.1 ግኝት፣ ለዶክተሮች በውል የተከፈለ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ያልቻለ፣

በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህራን እጥረት ሲያጋጥም እና የትርፍ ሰአት ስራ መሰራቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሚያስተምሩ መምህራን በማዕረጋቸው መሰረት በክሬዲት ሰዓት (Credit hours) ክፍያ እንደ ሚከፈል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠ.ሚ ጽ/ቤት ጥር 13/2003 ዓ.ም በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በዋቸሞ በዩኒቨርሲቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተለያዩ ኮርሶችን ለሚሰጡ ዶክተሮች ውል በመግባት ለእያንዳንዳቸው በወር ብር 40,000.00 በድምሩ ብር 428,100.00 ለተከፈላቸው ክሬዲት ሰዓቱ ባለመገለጹ በውሉ መሠረት ስለመከፈሉ የክፍያዉን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም ፡፡

መለያ ቁጥር	ቀን	የቮቸር አይነት	የቮቸር ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
57	30/05/2009	PV	0043854	6251	40,000.00
794	30/05/2009	PV	0042083	6251	40,000.00
231	30/07/2009	PV	397657	6251	40,000.00
235	30/07/2009	PV	397652	6251	40,000.00
236	30/07/2009	PV	397655	6251	40,000.00
800	30/10/2009	PV	397921	6251	158,100.00
415	04/02/2009	PV	0040682	6251	70,000.00
				ድምር	428,100.00

3.8.2 ስጋት፤

በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ መፈፀም ይገባል፡፡ ለእያንዳንዱ ክፍያ ክሬዲት ሰዓቱ በትክክል ተገልጾ የክፍያው ትክክለኛነት ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይከሰት ጥንቃቄ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

3.8.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የሀገርቱ የትኩረት አቅጣጫ የሆነውን የሐኪም ቁጥር እንዲጨመር ለማድረግ የራሱን አስተዋጾ ለማበረከት የህክምና ትምህርት ቤት ከፍቶ ተማሪዎችን እያስተማረ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጅ ተማሪዎቹ መማር ያለባቸው በAssitant Professor ማዕረግ ባላቸው የህክምና ባለሙያዎች በመሆኑ፣ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያሉት ስፔሻሊስት ሀኪሞች ቁጥር በጣም አነስተኛ በመሆኑ እና ከዚህ ባለፈ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የህክምና ባለሙያዎች ቁጥር በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም የተነሳ በሀገር እና በዓለም አቀፍ ጋዜጣ የቅጥር ማስታወቂያ ቢያወጣም መምህራኖች ሊያገኝ አልቻለም ብለዋል፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ አንገብጋቢ እና ጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት በልዩ ውሳኔ በAssitant Professor ማዕረግ ከመማር ማስተማር በተጨማሪ የህክምና አገልግሎት ጭምር እንዲሰጡና በበዓል እና በሳምንት መጨረሻ ቀናት ላይ ገብተው በሽተኞችን እንዲያዩና እንዲያማክሩ 30 ቀን ቢያንስ በቀን 12 ሰዓት እና በሰዓት በAssitant Professor Rank ውል ገብተው እንዲሰሩ እንዲደረግ ተወስኖ ተፈፃሚ እየሆነ መሆኑን እየገለፅን ለዚህም ሲቪል ሰርቪስ ሚንስቴርን ለማስፈቀድ በሂደት ላይ መሆናችንን እንገልፃለን ብለዋል፡፡

3.9.1 ግኝት፣ያለአግባብ የተከፈለ የኪስ ገንዘብ ክፍያ፣

በመማር ማስተማር ላይ የነበሩ መምህራን በአገር ውስጥ የትምህርት እድል በሚያገኙበት ጊዜ በፊት ሲከፈላቸው ከነበረው በተጨማሪ አዲስ አበባ ላሉ ብር 1700.00 ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ብር 1350.00 የቤት፣ የትራንስፖርት አበል እና ለጽህፈት

መሣሪያ እንደሚከፈላቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለኦዲት ከተመረጡት የወጪ ቫውቸሮች መካከል አቶ አቤኔዘር ግርማ ከየካቲት-ሰኔ/2009 በየወሩ ብር 1,700.00 መውሰድ ሲገባቸው፣ ብር 3,500.00 የሚከፈላቸው በመሆኑ በልዩነት ብር1800*5 ብር 9,000.00 እና አቶ ፍቃዱ ወየሳ ከየካቲት-ሰኔ በየወሩ ብር 1,350.00 መውሰድ ሲገባቸው ብር 4,050.00 የሚከፈላቸው በመሆኑ በልዩነት ብር 2,700*5 13,500.00 በድምሩ ብር 22,500.00 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3.9.2 <u>ስጋት፤</u>

- የወጡ ሕጎች፤ደንቦችና የአፈፃፀምመመሪዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- መንግስትን ለተጨማሪ ወጭ ሊዳርግ ይችላል፡፡

3.9.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- በመመሪያው መሰረት ክፍያ መፈጸም ይገባል፡፡
- ከባለሙያዎቹ ያለአግባብ የተከፈላቸው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- በናሙና ከታዩት ውጭ ያሉትንና የ2009 በጀት ዓመት በአግባቡ መከፈሉ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

3.9.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የኋላ ቀሪ የኪስ ገንዘብ እንዲከፍል ሲጻፍ 1350*3=4050 የሆነ እና የወር እና የቀናት ተሰልቶ ሲሰራ የተፈጠረዉ ልዩነት እንጂ እላፊ የተከፈለ አለመሆኑን ማስተካከያ የተደረገበት መሆኑን ጭምር እንገልጻለን ብለዋል፡፡

3.9.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፤</u>

የኋላ ቀሪ የኪስ ገንዘብ እንዲከፍል ሲጻፍ የወር እና የቀናት ሂሰብ ተሰልቶ ሲሰራ የተፈጠረ ልዩነት ከሆነ ማስተካከያ የተደረገበት ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.10.1 <u>ግኝት ፣ ያለአግባብ የተከፈለ እና ያልተቀነሰ የሥራ ግብር ሂሳብ፣</u>

በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን እጥረት ሲያጋጥም የተጨማሪ ሰዓት ክፍያ በአካዳሚክ ማዕረጋቸው መሰረት በመክፈል እንደሚያስተምሩ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሰረት ኦዲት ሲደረግ፣ የዩኒቨርሲቲው የመደበኛ ተማሪዎች የአካዳሚክ ዓመት (ካላንደር) 16 ሳምንት መሆኑ እየታወቀ የ18 ሳምንት ክፍያ እንዲከፈላቸው በመደረጉ፣ በተጨማሪም የገቢ

ግብር አዋጅ 979/2008 ክፍል ሁለት አንቀጽ 10 (1) ማንኛውም ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ከደመወዝ ጋር ተደምሮ የስራ ግብር ሊከፈልበት እንደሚገባ ተመልክቷል። ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች የትርፍ ሰአት ክፍያ በቀን 19/08/09 በወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር 590843 በተከፈለው ክፍያ ላይ የትርፍ ሰዓት ክፍያው ከደመወዝ ጋር ሳይደመር የሥራ ግብር እንዲቀነስ በመደረጉ ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተጣራ ብር 477,669.28 የተከፈለ መሆኑ ታውቋል።

3.10.2 <u>ስጋት፤</u>

- የወጡ ሕጎች፤ ደንቦችና የአፈፃፀም መመሪዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል።
- መንግሥት የሚገባውን ያህል ገቢ ላይሰበስብ ይችላል።

3.10.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- በአካዳሚክ ዓመቱ መሰረት ክፍያ መፈጸም ይገባል።
- በአዋጁ መሠረት የሥራ ግብር ሊሰበሰብ ይገባል።
- ከባለሙያዎቹ ያለአግባብ የተከፈላቸው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል።

3.10.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የተከፈለው ክፍያ የትርፍ ሰዓት ሳይሆን ለመምህራን በመመሪያው መሰረት በውል /over load/ የሰሩበት በዉል መሠረት የተከፈለ ነው። ይህን ክፍያ ለመፈጸም መነሻውም የዩኒቨርሲቲው ሌጅስሌሽን በሚያዘው መሰረት እና ከዚህ በፊት አሠራሩን ጠብቆ እንደሚከፈለው እየተከፈለ ነው ብለዋል።

3.11.1 <u>ግኝት፣ ከትርፍ ሰዓት ክፍያ የሥራ ግብሩ ያልተቀነሰ፣</u>

በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን እጥረት ሲያጋጥም እና ለተከታታይ ትምህርት በአካዳሚክ ማዕረጋቸው መሰረት በመክፈል እንደሚያስተምሩ ይታወቃል። በዚህም መሰረት ኦዲት ሲደረግ፣ የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ክፍል ሁለት አንቀጽ 10 (1) ማንኛውም ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ከደመወዝ ጋር ተደምሮ የሥራ ግብር ሊከፈልበት እንደሚገባ ቢገልጽም የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተለያየ ቀን እና በተለያየ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር በተከፈለው ክፍያ ከደመወዝ ጋር ሳይደመር የሥራ ግብር እንዲቀነስ

በመደረጉ ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተጣራ ብር 648,661.80 የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3.11.2 ስጋት፤

- የወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና የአፈፃፀም መመሪዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- መንግሥት የሚገባውን ያህል ገቢ ላይሰበስብ ይችላል፡፡

3.11.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- በአዋጁ መሠረት የሥራ ግብር ሊሰብሰብ ይገባል፡፡
- ከባለሙያዎቹ ያለአግባብ የተከፈላቸው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.11.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ይህ ክፍያ የትርፍ ሰአት ክፍያ ሳይሆን የተከታታይ ትምህርት በውል ለሚያስተምሩ መምህራን በትምህርት ደረጃቸዉ መመሪያ በሚፈቅደዉ መሰረት በሴሚስተር መጨረሻ በጥቅል ክፍያ መጠን ከዩኒቨርሲቲው ጋር በገቡት ውል መሠረት ፔሮል ተዘጋጅቶ የስራ ግብር በውሉ መሰረት ተቀንሶ የተከፈለ ሲሆን ከዚህ የተሻለ አሰራር ካለ ግን ወደፊት በሚሠጠው አቅጣጫ መሠረት የምናስተካክል መሆኑን እንገለጻለን ብለዋል፡፡

3.12.1 ግኝት፣ በመስክ ላልነበሩ የተከፈለ የውሎ አበል፣

የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ ሰኔ 2004 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 4 የውሎ አበል ተመንና አከፋፋል መሰረት ኦዲት ሲደረግ፣ በ2008 በጀት ዓመት አጠቃላይ የንብረት ቆጠራ ለተሳተፉ ሠራተኞች ለእያንዳንዳቸው የ20 ቀን የውሎ አበል እንዲከፈላቸው ሲደረግ፣ ባለሙያዎቹ በመስክ ሥራ ላይ ሳይሆኑ የውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ 2 በዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ ቀስመው እንዲመጡና ግንዛቤ እንዲያገኙ የተላኩበት በሚል የመስክ ስራ እንደቆዩ ተደርጎ በመፈረምና የሚመለከተውም ኃላፊ ከህግ ውጭ የሚያረጋግጥ በመሆኑ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0175258 በ10/04/2009 የቀን ውሎ አበል ብር 84,591.30 እና የትራንስፖርት ብር 3,220.00 በድምሩ ብር 87,812.30 የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.12.2 <u>ስጋት፤</u>

- በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- በመስክ ስራ ላይ ሳይሆን የመስክ ስራ ብሎ ፎርም መሙላትና አበል መውሰድ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- የመስክ ስራ ሳይሄዱ የትራንስፖርት ደረሰኝ በማቅረብ የመንግስትን ገንዘብ አላግባብ መውሰድ ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በመስክ ስራ ያልነበረን ባለሙያ የመስክ ስራ ነው ብሎ በመፈረም ማረጋገጫ በመስጠት የመንግስትን ገንዘብ ያለአግባብ እንዲወስድ ማድረግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.12.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ መፈፀም ይገባል፡፡
- ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች ተመላሽ ሊደረጉ እና ለወደፊትም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የሚከፈሉ ክፍያዎች ኢኮኖሚካል ወጭ ቆጣቢና ስራዎችን መሰረት ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

3.12.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- ሠራተኞቹ የወሰዱትን አበል እንዲመልሱ በደብዳቤ ትዕዛዝ ተሠጥቷል፡፡
- ተግባራዊነቱንም በቅርበት ተከታትለን የምናስፈፅም ይሆናል ብለዋል፡፡

3.13.1 <u>ግኝት፣ የውሎ አበል ክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፣</u>

የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ሰኔ 2004 ዓ.ም በወጣው የአበል አከፋፈል መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የሂሳብ ማወራረጃ ቅፅ 2 ላይ መሞላት የሚገባቸው ሠራተኛው ለጉዞ የተነሳበት እና የደረሰበት ሰዓትና ቀን እንዲሁም ለሥራ የቆየባቸው ቦታዎች ሳይሞሉ በተሰብሳቢ የተያዘውን የገንዘብ መጠን ብቻ በመውሰድ ለኦዲት ከተመረጡት ውስጥ በድምሩ ብር 209,279.00 በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ እና በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተከፍሎ በመገኘቱ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3.13.2 ስጋት፣

- ተገቢው መረጃ ባለመሞላቱ ክፍያው በተመኑ መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡
- አስፈላጊው መረጃ ሳይሞላ የሚከፈለው ክፍያ ከህግና መመሪያ ውጭ ሊሆን ይችላል ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.13.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጽም የውሎ አበል ክፍያን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ዝርዝር መረጃ በቅፁ እንዲገለፅ እና እንዲወራረድ በማድረግ ሂሳቡ ከተሰራ በኂላ ተጨማሪ ክፍያም የሚስፈልጋቸው ከሆነም እንዲወስዱ ተመላሽ ካለባቸውም እንዲመልሱ ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ የተጠቀሰውም የውሎ አበል ሂሳብ ሊጣራና ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡

3.13.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በዋና ግቢ ሰራተኞች በቅጽ አንድ በተሰብሳቢ አበል በሚሄዱ ሰአት በሚያወራርዱበት ወቅት ሁሉንም ፎረማሊቲ ላያሟሉ ይችላሉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የአስር ቀን በተሰብሳቢ በሚወስዱበት ሰአት የሚያወራርዱት ከአስር ቀን በኂላ ስለሆነ ቅጽ ሁለት ማወራረጃው የሚያያዘዉ በተሰብሳቢዉ ላይ ነዉ፡፡ አብዛኛዉ ሰራተኛ እያንዳንዱ ቅጽ ላይ ያለውን የመሙላት ክፍተት እንዳለ ተገንዝበናል፡፡ ለቀጣይ ማንኛዉም ቅጽ ላይ በስርአቱ መሞላት እንዳለበት እንከታተላለን ብለዋል፡፡

3.14.1 ግኝት፣ በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል፣

የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ ሰኔ 2004 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 4 የውሎ አበል ተመንና አከፋፋል መሰረት የተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ባለሙያዎቹ በመስክ ስራ እንደሆኑ በተሞላው የመንግስት ሠራተኞች ውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ 2 መሰረት በዱራሜ ካምፓስ ያለ አግባብ ብር 3,640.55 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የአበል አከፋፈል ስርአቱ የአበል ማወራረጃ ቅጽ 2 የመስክ ስራ እንደሆነ የተሞላ እና የተፈረመ ቢሆንም ባለሙያዎች

ከሚሰሩት ስራ እና ከሚቆዩበት ጊዜ ጋር ሲታይ ተአማኝነት የሌለው መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

3.14.2 ስጋት፣

- በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- ያለአግባብ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ከሚሰራው ስራ ጋር ተመጣጣኝ የማይሆን ቀን በመሙላት የሚከፈል ውሎ አበል ክፍያ ባለሙያንም ይሁን የበላይ ሀላፊን ተጠያቂ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.14.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ መፈፀም ይገባል፡፡
- ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች ተመላሽ ሊደረጉ እና ለወደፊትም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.14.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በዱራሜ ካምፓስ አለአግባብ የተከፈለ የተባለዉን የውሎ አበሉ ማወራረጃ ሰነድ መነሻና መመለሻ ቀን ፊዚካል ከሰነዱ ጋር ከኦዲተሮቹ ጋር ያልተናበቡ ሲሆን የተከፈለዉ አበል በስራ ላይ በቆዩበት ቀናት ጋር ሲነፃጸር ተአማኝነት የለዉም ተብሎ ለቀረበዉ አስተያየት ሁሉም የስራ ክፍሎች አስተያየቱን በቅንነት በመቀበል የሰራተኞች ውሎ አበል ሲፈርሙ እንደስራዉ ክብደትና ቅለት በማገናዘብ መአከላዊ በማድረግ የመንግስትን ሀብት በተገቢዉ ሁኔታ መጠቀም አለብን (አለባቸዉ) ብዬ አምናለሁ፡፡በተጨማሪ አላግባብ የተከፈለዉ ዉሎ አበል ሰነዱን ከተናበብን በኋላ የማይገባቸዉን ጥቅም ሰራተኞቹ ማግኘት ስለሌለባቸዉ ለመንግስት ተመላሽ እንዲደረግ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

3.15.1 ግኝት፣ ላልተፈቀደ የበላይ ኃላፊነት የተከፈለ የቀን ውሎ አበል፣

የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል ሰኔ 2004 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 4 በወጣው የውሎ አበል ተመንና አከፋፋል መሰረት እየተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ ለዱራሜ ካምፓስ እና ለጤና ሳይንስ ኮለጅ አስተባባሪ

የጸደቀ /የተፈቀደ/ የበላይ ኃላፊዎች /ተሿሚዎች/ የሥራ መደብ ሳይኖር፣ በበላይ ኃላፊዎች የቀን ውሎ አበል መሰረት ያለአግባብ ብር 36,638.00 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.15.2 ስጋት፣

- በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡
- ያለአግባብ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነት ሊያሥከትል ይችላል፡፡

3.15.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ መፈፀም ይገባል፡፡ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች ተመላሽ ሊደረጉ እና ለወደፊትም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.15.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የጤና ጥበቃ ሚንስቴር የፌዴራል ሆ/ሎችን እንዲያስተዳድር በአዋጅ ቁጥር 691/2010 እና የትምህርት ሚነስቴር ከፍተኛ ተቋማት እንዲያስፋፉ እና እንዲመራ በአዋጅ ቁጥር 69/2010 በተሰጠው ስልጠና መሠረት በ2015 የዩኒቨርሲቲ ሆ/ሎች መተዳደሪያ መመሪያ ላይ የሆ/ል አሰተዳደርን በ Chief Executive Director መደብ ከዩኒቨርሲቲዎች ምክትል ፕሬዝዳንት ማዕረግ ተግባራት እንዲወጣ በግልፅ ባስቀመጠው መሠረት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን እየገለፅን ለዚህም አፈፃፀም የምንጠቀመውን የዩኒቨርሲቲ ሆ/ሎች አመራር መመሪያ አባሪ ማድረጋችን እንገልፃለን ብለዋል፡፡

3.15.5 የኦዲተሩ አስተያየት፤

በስራ አመራር ምላሹ የጤና ጥበቃ ሚንስቴር የፌዴራል ሆስፒታሎችን እንዲያስተዳድር እና የትምህርት ሚነስቴር ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲያስፋፋ እና እንዲመራ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተግባራዊ የተደረገ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ሆኖም የሆስፒታል አሰተዳደርን በ Chief Executive Director መደብ በዩኒቨርሲቲዎች ምክትል ፕሬዝዳንት ማዕረግ በተመጣጣኝ ደረጃ የጸደቀ /የተፈቀደ/ የበላይ ኃላፊዎች/ ተሿሚዎች/ የሥራ መደብ ሳይኖር በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የተመደቡ ስለሆነ በበላይ ኃላፊዎች የቀን ውሎ አበል ልክ ተከፍሎ ለተገኘው መዋቅሩ እንዲሻሻል ተደርጎ ሲቪል ሰርቪስ ሚንስቴርን በማስፈቀድ ሊሰራ ይገባል፡፡

3.16.1 ግኝት፣ ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ፣

የመንግስት ሰራተኞች የቀን ወሎ አበል መመሪያ ሰኔ 2004 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 4 የውሎ አበል ተመንና አከፋፋል መሰረት እየተከፈለ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዱራሜ ካምፓስ የመንግስት ሰራተኞች ውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ 2 መሰረት በዱራሜ አበል አከፋፈል ብር 171.00 መከፈለል ሲገባው፣ በሐዋሳ የአበል መጠን ብር 202.00 የተከፈለ ሲሆን፣ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 156543 በ16/08/09 ብር 3,030.00፣ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 156584 በ07/09/09 ብር 2,304.00፣ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 156542 በ16/08/09 ብር 3,030.00፣ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 156541 በ16/08/09 ብር 3,030.00 ከደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን እና ከከምባታ ጠምባሮ ዞን ም/ቤት ለመጡ በሚል በድምሩ ብር 11,394.00 ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.16.2 ስጋት፣

- በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- ያለአግባብ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፡፡
- የመስሪያ ቤቱ ስራ ዱራሜ ሆኖ ሳለ ሐዋሳ ሆነው ሰርተዋል ብሎ የመንግስትን ገንዘብ መክፈል ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡

3.16.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ መፈፀም ይገባል፡፡
- ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች እንዲፈጸም ካደረጉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተመላሽ እንዲያደርጉ እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.16.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዱራሜ ካምፓስ ትምህርት አሰጣጡና ተቋማዊ ይዘቱ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ የደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች በካምፓሱ ጥያቄ መሠረት በዞኑ በወረዳዎች ላይ ዞረው ለሰሩበት የተከፈለ ውሎ አበል ሲሆን ከአመዘጋገብ ጋር ያለውን ስህተት ማስተካከያ የምናደርግ መሆኑን እንገልፃለን ብለዋል፡፡

3.16.5 የኦዲተሩ አስተያየት

በስራ አመራሩ ምላሽ የደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች በካምፓሱ ጥያቄ መሠረት በዞኑ በወረዳዎች ዞረው ለሰሩበት የተከፈለ ውሎ አበል መሆኑ ተገልጿል፡፡ ሆኖም ከሀዋሳ

ዱራሚ ከመጡ የአበል ክፍያ መጠን በዱራሚ ብር 171.00 እንጂ በሀዋሳ ብር 202.00 መሰላት የለበትም፡፡ በተጨማሪም ከዱራሚ ሀዋሳ በሚል ሄደው እንደሰሩ የሚገልፅ በመሆኑ የውሎ አበል ክፍያ በሚሰጥበት ጊዜ ስራው እንዲሰራ የታዘዘበት ደብዳቤ በሚወራረድበት ጊዜ ደግሞ ስራው በትክክል የተሰራ ለመሆኑ በሀላፊ እየተረጋገጠ ክፍያው ሊፈፀም ይገባል፡፡

3.17.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከተከፋይ ተቀናሽ (ዊዝሆልዲንግ ታክስ) ከአቅራቢዎች ሳይቀነስ የተከፈለ፣</u>

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የካቲት 2002 ዓ.ም በወጣው በገዥዎች ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣው መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 4 ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ላይ ተቀናሽ ተደርጎ ስለሚያዝ ታክስ ንዑስ ቁጥር 1 ማንኛውም ወኪል በሚፈጽመው ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ለአቅራቢው መከፈል የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ በማስቀረት በየወሩ ቀንሶ ያስቀረውን በሚቀጥለው ወር ውስጥ በታክሰ ከፋይነት በተመዘገበበት የታክስ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የፌዴራል መንግስት የገቢ የግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 53 ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት ንዑስ አንቀጽ 3. ግብር ተቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው በወሩ ውስጥ ተቀንሶ ቀሪ መደረግ የሚገባውን አጠቃላይ ሂሳብ በወሩ መጨረሻ ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሰቲው በ13/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 154224 የተለያዩ የቢሮ ዕቃዎችን ሲገዛ ብር 1,954,208.00 ክፍያ ሲፈጽም፣ ብር 33,986.20 ከተከፋይ ሂሳብ የሚቀነስ ገንዘብ (ዊዝሆልዲንግ ታክስ) ከአቅራቢዎች ሳይቀነስ ወይም ሳይሰበሰብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3.17.2 <u>ስጋት፣</u>

የመንግስት ህግና ደንብን ተከትሎ አለመስራት የመንግስት ግብር በአግባቡ እንዳይከፈል ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

3.17.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኝዉም ክፍያ ለአቅራቢዎች ሲከፈል ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለሚቀነስ ገንዘብ ደረሰኝ ተዘጋጅቶ ከአቅራቢዎች ሊቀነስ ይገባል፡፡ እስካሁን ሳይሰበሰብ የቀረው ገንዘብ ከድርጅቶቹ

ተሰበስቦ ለመንግስት ገቢ መሆን አለበት። ለወደፊቱም ይህ አይነት አሰራር እንዳይደገም በሥራ አመራሩ በኩል ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል።

3.17.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ድርጅቱ ቅድሚያ ክፍያ የወሰደ በመሆኑ 4253 ተሰብሳቢ ሂሳብ ሲቀናነስ እላፊ የተቀነሰ ስለነበር ሂሳቡን ለማስተካከል የተደረገ የሂሳብ ማስተካከያ የተሰራበት ነው። ድርጅቱ ቅድሚያ ክፍያ የወሰደበትና ያልወሰደበት ሁለት አይነት ግዢዎች በመኖራቸው ምክንያት የተፈጠረ ስህተት ነበር በአሁን ሰዓት ለድርጅቱ የመጨረሻ ክፍያ ሲከፈል የተስተካከለ መሆኑን እናሳውቃለን ብለዋል።

3.17.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በስራአመራር ምላሹ ላይ ቅድሚያ ክፍያ በአሁኑ ሰዓት ለድርጅቱ የመጨረሻ ክፍያ ሲከፈል የተስተካከለ መሆኑ ተገልጿል።ሆኖም የተስተካከለ ለመሆኑ ማስረጃው ቀርቦ ሊታይ ይገባል።

3.18.1 ግኝት፣ ከተከፋይ ተቀናሽ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልተቆረጠ፣

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 14.2 የመደበኛና የካፒታል የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈፀሙ የሚከተሉትን በማሟላት ይሆናል በሚለው ስር «ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት መመሪያ ቢያመለክትም የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢ ድረጀቶች ግዥ ሲፈጽም ከተከፋይ ሂሳብ ለተቀነሰ ገንዘብ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ ብር 170,604.15 ደረሰኝ ሳይቆረጥለት መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚመለከተዉ ቀረቧል፡፡

ቀን	የአቅረቢዉ ስም	የገንዘብ መጠን	የወጪማ ስመስከሪያ ቁጥር	ደረሰኝ የልተቆረጠለት ቅድመ ተቀናሽ	ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ተጨማሪ እሴት ታክስ	በድምሩ ደረሰኝ ያለተቆረጠለት
25/01/09	ጽጋ ተስፋዬ ብትን ጨርቅ አቅራቢ	390,420.00	496128	6,789.73	50,922.90	57,712.63
	ሀፍር ኤሌክትሮኒክስ እቃ አቅራቢ	335,400.00	158847	5,832.90	43,748.10	49,581.00
15/02/09	ጌታነህ ደነቀ የምግብ ቤት እቃ አስመጪ	333,500.00	496127	5,800.00	43,500.00	49,300.00
24/02/09	ናኖዳስ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ.የግል.ማህበር	46,300.00	158463	-	6,039.13	6,039.13

6/3/2009	የኢትዮጵያ ሞተርና ኢንጂነሪነገግ ኩባንያ(ሞኢንኮ)	15,361.00	157021	267.15	2,003.64	2270.79
12/4/2009	ኒያላ ሞተርስ	38,532.22	157054	668.00	5,032.60	5700.6
					ድምር	**170,604.15**

3.18.2 **ስጋት፣**

የመንግስት ህግና ደንብን ተከትሎ አለመስራት የመንግሰት ግብር በአግባቡ እንዳይከፈል ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

3.18.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ማንኛውም የመንግስት ሂሳብ በወጪ መመዝገብ የሚገባዉ ህጋዊ ደረሰኝ ሲቀረብለት ብቻ መሆኑ ታዉቆ ለወደፊቱም ይህ አይነት አሰራር እንዳይደግም በማኔጅመንቱ በኩል ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡

3.18.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

የአብዛኞቹ ድርጅቶች እና አቅራቢዎች ደረሰኞቹ በጊዜዉ ተቆርጠዋል ነገር ግን ከሰነድ ጋር ሳይያያዙ የቀረ በመሆኑ የተፈጠረ ክፍተት ስለሆነ በአሁኑ ሰዓት አብዛኞቹ ከሰነዶቹ ጋር ተያይዘዋል የተቀሩቱንም የምናሟላ ይሆናልብለዋል፡፡

3.18.5 **የኦዲተሩ አስተያየት፣**

በአሁኑ ሰዓት አብዛኞቹ ከሰነዶቹ ጋር ተያይዘዋል የተቀሩቱንም የምናሟላ ይሆናል ለተባለው የተያያዙትን ደረሰኞች በማስረጃነት ማቅረብ ይገባል፡፡

3.19.1 **ግኝት፣ የተሰበሰበው ታክስ ወቅቱን ጠብቆ ፈሰስ ያልተደረገ፣**

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የካቲት 2002 ዓ.ም ባወጣው በገዥዎች ተይዞ ስለሚክፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣው መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 4 ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ተቀናሽ ተደርጎ ስለሚያዝ ታክስ ንዑስ ቁጥር 1 ማንኛውም ወኪል በሚፈጽመው ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ለአቅራቢው መክፈል የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ በማስቀረት በየወሩ ቀንሶ ያስቀረውን በሚቀጥለው ወር ውስጥ

በታክስ ከፋይነት በተመዘገበበት የታክስ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የፌዴራል መንግስት የገቢ የግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 53 ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት ንዑስ አንቀጽ 3. ግብር ተቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው በወሩ ውስጥ ተቀንሶ ቀሪ መደረግ የሚገባውን አጠቃላይ ሂሳብ በወሩ መጨረሻ ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት ይላል፡፡ ይሆን እንጂ በዋቸሞ ዩኒቨርስቲው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከአቅራቢዎች የሰበሰበውን ከተከፋይ ተቀናሽ (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ) ብር 47,926.57 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 216,145.83 በድምሩ ብር 264,072.40 የሰበሰበውን ለገቢዎችና ጉምሩክ ሳያስተላልፍ በሪፖረት ተመዝገቦ ለመታየቱ ተረጋግጧል፡፡

3.19.2 ስጋት፣

የመንግስትን ህግና ደንብን ተከትሎ አለመስራት መንግስት በወቅቱ ሊያገኘው የሚችለውን ገቢ እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም ሆስፒታሉን ለቅጣት ወይም ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

3.19.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ሆስፒታሉ ከግብር ከፋዩ የተሰበሰበውን ታክስ በመመሪያው በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሚመለከተው የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በወቅቱ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ከግብር ከፋዩ የሰበሰበውን ግብር በሪፖረት ማሳየት አለበት፡፡

3.19.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የ2% እና የ15% በድምሩ ብር 264.072.40 ብቻ ወደ ገቢዎች ያልተላለፈው እና በTR ላይም ያልተመዘገበው እውነት ቢሆንም ችግሩ የሆስፒታሉ የፋይናንስ ባለሙያዎች አዳዲስና የተለያዩ ስልጠናዎችን ያልወሰዱ በፌዴራል አሰራር ግንዛቤ ችግር ስለነበረ የተፈጠረ ክፍተት ነው፡፡ ሆኖም ከላይ የተጠቀሰው ገንዘብ ለሚመለከተው ክፍል ባይተላለፍም ከዚህ በጀት ዓመት ላይ የምናስተላለፍ መሆኑን እያሳወቅን የቀጣዩን ስራ ግን በኦዲተሮች በተሰጠው አስተያየት መሰረት ደንቡን ተከትሎ እንዲሰራ ጥብቅ ክትትል እና ድጋፍ የሚደረግ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ ማስተካከያ ይደረጋል ብለዋል፡፡

3.20.1 ግኝት፣ ከመደበኛ በጀት ለተከታታይ ትምህርት የተከፈለ፣

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤቱ ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል:: በተጨማሪም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ብር 29,754.00 ከውስጥ ገቢ መከፈል የሚገባውን ከመደበኛ በጀት ለተከታታይ ትምህርት ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**

ተ.ቁ	ቀን	የወጭ ማስመከሪያ ቁጥር	የበጀት ምንጭ	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	30/10/09	431485	1800	6231	17,100.00
2	30/10/09	431474	1800	6231	12,654.00
				ድምር	<u>29,754.00</u>

3.20.2 ስጋት፣

- የመንግስትን በጀት ከደንብና መመሪያ ውጭ መጠቀም የመንግስት መመሪያን ከመጣሱም በላይ ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- ውስን የመንግስት በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

3.20.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ከተፈቀደለት የሥራ ዘርፍ ውጭ ባልተፈቀደለት በጀት ክፍያ እንዳይፈፅም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.20.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የውስጥ ገቢና የመደበኛ በጀት ለ2010 በጀት አመት ሙሉ ለሙሉ ተለይቶ ለየብቻ እንዲሰራ ተደርጓል ብለዋል፡፡

3.21.1 ግኝት፣ ያለሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ የተገኘ፣

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 3 መሠረት የሂሳብ እንቅስቃሴዎች በየመደባቸው ተለይተው መመዝገብ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ እንቅስቃሴዎች በመመሪያው መሠረት መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በዋና ግቢ ብር 3,405,421.00 እና በዱራሜ ካምፓስ ብር 36,911.00 በድምሩ የብር 3,442,332.00 ወጪዎች በተገቢው የሂሳብ መደባቸው ሳይመዘገቡ መገኘታቸው ተረጋግጧል፡፡ **ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**

ቀን	የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የተመዘገበበት የሂሳብ መደብ	መመዝገብ የነበረበት	የወጪ ምክንያት	
02/06/09	591110	6216	6218	የማገዶ እንጨት ግዥ	3,075,488.00
25/01/09	496128	5006	5059	የደንብልብስ ግዥ	50,922.90
25/01/09	496128	5059	5006	የደንብልብስ ግዥ	6,789.73
12/01/09	149727	6216	6218	የማገዶ እንጨት ግዥ	272,220.00
23/09/09	33[illegible]924	6255	61114	ግቢ ለማስዋብ ለቀን ሰራተኞች የተከፈለ ክፍያ	14,880.00
23/09/09	332925	6255	6114	ግቢ ለማስዋብ ለቀን ሰራተኞች የተከፈለ ክፍያ	15,631.00
30/10/09	586283	6255	6114	ለችግኝ ተከላ ጉረጓድ የቆፈሩበት ለቀን ሰራተኞች የተከፈለ	2,400.00
5/08/09	332788	6251	6114	ትራንስፎርመር ለማስገባት የቀን ስ[illegible] ለሰሩ ሰራተኞች የተከፈለ	4,000.00
				ድምር	3,442,332.63

3.21.2 ስጋት፣

የወጪ ሂሳቦች በተገቢው መደባቸው አለመመዝገባቸው የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ ከወጪ ቀሪያቸውን እንዳያሳዩ እና የበጀት አጠቃቀሙንም የተዛባ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.21.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት ለወጪው በጀት መያዙንና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ በተገቢው የሂሳብ መደብ መያዛቸው መረጋገጥ ይገባዋል፡፡ የወጪ ሂሳቦች በተገቢው የሂሳብ መደባቸው አለመመዝገባቸው የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ ከወጪ ቀሪያቸውን እንዳያሳዩ እና የበጀት አጠቃቀሙንም የተዛባ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት የማገዶ እንጨት ግዥ በሂሳብ መደብ 6218 (ለሌሎች አቅርቦቶች) በሚለው መመዝገብ ሲገባው፣ በሂሳብ መደብ 6216 ለምግብ በሚል ተመዝገቦ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በትክክለኛው የሂሳብ መደብ (6218) ቢመዘገብ ኖሮ ለመደቡ ከተደለደለው በጀት በብር 2,881,161.95 ከበጀት በላይ መጠቀማቸውን ያረጋግጣል፡፡

3.21.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

6218 እንደ 6216 በተመዘገበዉ ከዚህ በፊት በተሰጠን የኦዲት አስተያየት ተከትለን እየመዘገብን ስለሆነ ይህም ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚመጡ አስተያየቶች ችግር ሆኖብናል ለወደፊቱ ግን የአሁኑ ኦዲተሮች በሰጡት መሠረት እናስተካክላለን ብለዋል፡፡

3.22.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የህንጻ ግንባታን በተመለከተ (አማካሪ ድርጅት)፣</u>

ሰኔ/2002 በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 7 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 5 (ሀ) የመንግሥት መ/ቤት ለግንባታ ዘርፍ ክፍያ የሚፈፀመው የሥራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ መሆን እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በመመሪያው መሠረት ክፍያ መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በድምሩ ብር **90,157,493.32** የተከፈለ ሲሆን፤ ክፍያው በተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት መሀንዲስ እና በህ/ሥ/ተቋራጮች በተዘጋጀ የክፍያ ሰርተፍኬት እና በሥራ አመራሩ ፀድቆ እንዲከፈል መደረጉ ተረጋግጧል፡፡

3.22.2 <u>ስጋት፣</u>

- መንግሥት ያወጣቸው አዋጅ፣ ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች ሥራ ላይ እንዳይውሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- የመንግስት እና የህዝብ ገንዘብ ለታለመለት አላማ መዋሉን ማረጋገጥ አያስችልም፡፡

3.22.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- በመንግሥት ታምነው በወጡ አዋጅ፣ ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች መሠረት ክፍያዎች ተረጋግጠው መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡
- የመንግስት እና የህዝብ ገንዘብ ለታለመለት አለማ እንድዉል የዉስጥ ቁጥጥር ማጠናከር ይገባል፡፡

3.22.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት በአስሩ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች በከተማና ቤቶች ልማት ሚ/ር በጸደቀ ቁርጥ ዋጋ ግንባታቸዉ የሚከናወን ሲሆን እያንዳንዱ ስራ ዋጋ ቀድሞም የጸደቀ ነዉ፡፡ ስለሆነም በጸደቀዉ ቁርጥ ዋጋ መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎች ሲሆን በ2010 በጀት ዓመት በአሁኑ ሰአት ያለፉ ስራዎችንም ጨምሮ በትክክል መሰራታቸዉን በአማካሪ መሀንዲስ ክፍያዎች ተረጋግጠዉ የተፈፅሙ ሲሆን በዚህ መልኩ ማስተካከያ አድርገናል ብለዋል፡፡

3.23.1 ግኝት፣ ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ ክፍያ የተፈጸመ፣

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጂናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት መመሪያ ያዛል፡፡ይሁን እንጂ የዩንቨርስቲው የ2009 በጀት ዓመት ክፍያዎች መመሪያውን ተከትለው የተፈፀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ብር 6,356,593.80 በዋና ግቢ ክፍያው በማስረጃነት መቅረብ የሚገባው የሽያጭ ደረሰኝ /Cash sale invoice/ መሆን ሲገባው፣ የዱቤ የሽይጭ ደረሰኝ /Credit sale invoice/ እንዲቀርብ በማድረግ ሂሳቡ እንዲወራረድ መደረጉን ለማረጋገጥ ተችሏል ፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተሉ ቀረቧል፤-

ተ.ራ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የድርጅቱ ስም	የክፍያዉ አይነት	በዱቤ ሽያጭ የተከፈለዉ የገንዘብ መጠን
1	28/05/09	157107	ነጋቲ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ	የተማሪዎች ፈራሽናትራስ ለመግዛት	4,004,658.24

2	26/09/09	154160	ረጅ ሳሙናና ድተረጃንት	የጽዳት እቃዎች ለመግዛት	244,756.80
3	15/07/09	591190	ሀይሌ ሪዞረት	ለስልጠና አገልግሎት የተገዛበት	323,640.59
4	26/09/09	154157	የኢትዮጲያ መደሀኒት ፈንድ ኤጀንሲ	የሀክምና እቃና መደሀኒት ግዢ	174,984.57
5	26/09/09	154174	አባዲር ሶፒንግ ሴንተር ፐልሲ	ኤር ፍሬሽ ለመግዛት	214,500.00
6	26/09/09	154169	ናኖዳስ ንግድና እንዱስትሪ	ፎቶ ኮፒ ቶነር ግዢ	279,600.00
7	26/09/09	154173	አኢንተር ኢምሬትስ ኢትዮ እንዱስትሪያል	ዲክቶል(የጽዳት እቃ የተገዛበት)	175,200.00
8	25/09/09	154165	ናኖዳስ ንግድና እንዱስትሪ	አላቂ የቢሮ እቃዎች ግዢ	939,253.60
				ድምር	6,356,593.80

3.23.2 ስጋት፣

በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ሂሳብ ማወራረድና መመዝገብ ሂሳቡ በድጋሚ ክፍያ ሊጠየቅበት የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ከመቻሉ በተጨማሪ ከድርጅቶቹ ለሚፈለግ የመንግስት ግብርና ታክስ ክትትልና ቁጥጥር አመቺ ላይሆን ይችላል፡፡

3.23.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ሂሳቡ በወጪ ሊመዘገብ የሚገባው ህጋዊ የሽያጭ ደረሰኝ ሲቀርብለት በመሆኑ ተገቢው ደረሰኝ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች ህጋዊ ደረሰኝ ሲቀርብላቸው ብቻ በወጪ እንዲመዘገቡ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.23.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- መመሪያዉ ስለሚፈቅድ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ /credite sales invoice/ ሲያቀርቡ ክፍያ የተፈጸመባቸዉ ቢሆንም የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞችን ከድርጅቶቹ እየሰበሰብን በማያያዝ ላይ እንገኛለን፡፡
- በወቅቱ የመደኃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ በፊት በዱቤ የተወሰደ የመደኃኒት በዱቤ ገንዘብ ካልተመለሰ አልሰጥም ሌላ መደኃኒት በተጨማሪ አልሰጥም በማለቱ ለበሽተኞች ሌላ መደኃኒት አልሰጥም በማለቱ ደረሰኙን ድርጅቱ

እስከሚሰጥ ድረስ የተከፈለ ስለሆነ ደረሰኙን ተከታትለን የምንወስድ መሆኑን እንገልፃለን ብለዋል፡፡

3.24.1 ግኝት፣ለክፍያው ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ የተፈጸመ፣

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 970/2008፣ በፋይናንስ አስተዳደር ሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 እና በፌዴራል መንግሰት የሂሳብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለማንኛውም ወጪ ክፍያ መፈጸም የሚገባው ተመጣጣኝ የክፍያ ደረሰኝ በማስረጃነት ሲቀርብ ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል። ይሁንና የዩኒቨርስቲው የወጪ ሂሳብ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፈ መሆኑ እየተረጋገጠ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለተለያዩ ወጪዎች ብር 4,386,682.10 ሲከፈል ለወጪው ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

3.24.2 ስጋት፣

- ዩኒቨርስቲው ለፈፀመው ክፍያ ማስረጃ ባለመቅረቡ የክፍያው ትክክለኛነት ላይረጋገጥ ይችላል ፡፡
- አገልግሎቱን ከሰጡት ድርጅቶች ክፍያ መፈፀሙን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ ገንዘቡ ለባለመብቱ ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡
- የመንግሥት ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡

3.24.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርስቲው ክፍያ ለፈፀመባቸው አገልግሎቶች መቅረብ የሚገባው የከፍያ ማስረጃ እንዲቀርብ መደረግ ይገባዋል። ለወደፊቱም ክፍያ ለሚፈፀምበት አገልግሎትም ሆነ ዕቃ ግዥ ለወጪው ተመጣጣኝ የክፍያ ማስረጃ መቅረቡ ሲረጋገጥ ሂሳቡ በወጪ መመዝገብ የሚገባው በመሆኑ የሥራአመራሩ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል።

3.24.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የመብራት የውሀና የቴሌኮም ክፍያዎች ጊዜ የማይሰጡ የመንግስት መ/ቤቶች በመሆናቸው በወቅቱ ያልተያያዙ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ አብዛኞቹን ደረሰኞች አያይዘን እንገኛለን የተቀሩትን ደረሰኞችን ተከታትለን እናቀርባለን ብለዋል፡፡

3.25.1 ግኝት፣ተከታታይ ቁጥር በሌላቸው ደረሰኞች የተከፈለ ክፍያ፣

ዩኒቨርሲቲው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነሀሴ 2001 ዓ.ም ስለደረሰኝ አያያዝ፣አጠባበቅና ቁጥጥር ባወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም የግዥ እና የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፅም የክፍያው (የወጪው) ማስረጃ ተከታታይ ቁጥር ያለው እና የድርጅቱ ስምና አድራሻ አብሮ የታተመ ትክክለኛ ፋክቱር/ደረሰኝ/ መሆኑን እያረጋገጠ ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል ይላል፡፡ በዚህ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በብር 60,817.71 ለተማሪዎች የምግብ ግብአት እና ለመስተንግዶ የወጣው በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዱራሜ ካምፓስ ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**

ተ.ቁ	ቀን	የወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሒሳብ መደብ	የተከፈለ ክፍያ
1	17/08/09	156545	6233	4,824.00
2	27/10/09	396523	6216	47,488.71
3	20/07/09	332713	6233	4,809.00
4	27/0709	156533	6233	3,696.00
			ድምር	**60,817.71**

3.25.2 ስጋት፣

የመንግሥትን ህግና ደንብ ሳይከተሉ የሚሰሩ ድርጅቶችን የሚያበረታታ፣ ድርጅቶቹ ገቢያቸውን እንዲደብቁና የሚጠበቅባቸውን ግብር በአግባቡ እንዳይከፍሉ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

3.25.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለተመለከቱት ክፍያዎች አግባብ ያለው ደረሰኝ ከአቅራቢዎቹ ቀርቦ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ሊያያዝ ይገባል፡፡

3.25.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ከሰነዱ ጋር የተያያዙ የሽያጭ ደረሰኞች በመለየት ከዋና ኦዲት የተሰጠውን አስተያየት በመቀበል ተገቢ ማስተከክያ እንደርጋለን ብለዋል፡፡

3.26.1 ግኝት፣ ለኦዲት ያልቀረቡ ማስተካከያ የተሰራለት እና የወጪ ሂሳብ ሰነድ፣

የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የፌደራል ዋና ኦዲተር የመስሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ወይም የፌደራል ዋና ኦዲተር ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አስፈላጊ የሚመስሏቸዉን መጽሀፍት፤ መዘክሮች፤ መዝገቦች፤ ሰነዶችና ሌሎች የጽሁፍ እና የቃል መረጃዎች ሁሉ ሲጠይቁ የተጠየቀዉ ግለሰብ፤ ሰራተኛው ወይም ባለስልጣን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት አዋጁ ቢያመለክትም፣ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ ኦዲት ሲደረግ፣ ማስተካከያ (Adjustment) በሚል ብር 96,728,320.73 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ (JV) ላይ የማስተካከያ ሂሳብ ከማለት በስተቀር ማስተካከያ የተሰራለትን የወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ ቁጥር፣ ቀንና የገንዘብ ልክ በመጥቀስ ማጣቀሻ ስላልተፃፈበት ማስተካከያ የተደረገውን ወጪ እና የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 38,938,099.53 የወጪ ሂሳብ ሰነዶች በድምሩ ብር 135,666,420.26 ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሊቀርቡ አልተቻሉም፡፡

3.26.2 ስጋት፣

ሰነዶቹ ባለመቅረባቸው የተነሳ የተከፈለው ክፍያ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3.26.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በዋናው ግቢ ማስተካከያ የተደረገባቸው የወጪ ማስመስከሪያዎች በግልጽ ተዘርዝረው መቀመጥና ሲጠየቁም ተዘርዝረው ሊቀርቡ ይገባል፡፡ እንዲሁም በሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለኦዲት የተጠየቁት ማስረጃዎች በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ ስሂሳቦቹ ትክክለኝነት ማረጋገጥ አያስችልም፡፡

3.26.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- በ2009 በጀት ዓመት ላይ የንግስት እሌኒ መታሰቢያ ሆስፒታል እና ዱራሜ ከምፓስ የራሳቸዉ የሆነ IBEX code የሌላቸዉ በመሆኑ ማለትም የራሳቸዉ የሆነ በጀት

ተለይቶ ባለመፈቀዱ ምክንያት እና የውስጥ ገቢና መደበኛ በጀት በምዝገባ ወቅት በመቀላቀሉ ማለትም 1900ና 1800 IBEX ባለመኖሩ የተነሳ ለአንዳንድ የወጪ መደቦች ላይ ችግር በመፍጠሩ ለዚህ መፍትሄ ይሆን ዘንድ JV ምዝገባ ማስተካከያ ተሰርቷል፡

- ከህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የ38,938,099.53 የውጪ ሂሳብ ሰነዶች ለኦዲት ስራ እንዲቀርቡ ተጠይቀው ያልቀረቡ የሚለውንም በሚመለከት
    - በወቅቱ ዩኒቨርስቲው ሆ/ሉ ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት የቢሮዎች መቀያየር የእድሳተ ስራ የነበረ መሆን ከክፍል ወደ ክፍል ሲሄድ የሰነዶች መዘበራረቅ፣
    - የፋይናስ ሰራተኞች አደራጅቶ ያለመያዝ የእውቀትና የሰው ሃይል እጥረት አዲስ መሆን፤
    - የሰነዱ ክፍል ሰራተኛ ለብዙ ወራት በህመም መቆየት ችግሮች ተደምሮ ይህንን ክፍተት የፈጠረ ሲሆን አሁን ግን ቀደም ሲል ከቀረበው በተጨማሪ ሁሉን ማለት በሚችል መልኩ ሰነድ ተለቅሞ በተጠየቀው መሰረት እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ በቀጣይ በሚደረገዉ ኦዲት ሆነ አሁን የሚፈለግ ከሆነ መለየት የሚቻል መሆኑን እንገልፃለን ብለዋል፡፡

3.27.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በሂሳብ መዝገብ (TR) ሁለት ጊዜየተመዝግቦ የተገኘ የወጪ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 3 መሠረት የሂሳብ እንቅስቃሴዎች በየመደባቸው ተለይተው መመዝገብ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ የዩኒቨረሲቲው የሂሳብ አመዘጋገብ በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24/12/08 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 14663 ብር 169,200.00 ለዩኒቨርሲቲው አገልግሎት የሚውል የደንብ ልብስ ለመግዛት፣ በ27/12/08 ለዩኒቨርሲቲዉ አገልግሎት የሚውል የጽዳት ዕቃዎችን ለመግዛት ብር 87,018.12 እና በ02/02/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 496121 የትርፍ ሰአት ክፍያ ብር 491,374.00 ክፍያ የተፈጸመው በድምሩ ብር 747,592.12 በሂሳብ መዝገብ (TR) ሁለት ጊዜ በወጪ የተመዘገበ እና ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

3.27.2 **ስጋት፣**

የወጪ ሂሳቦች በትክክል አለመመዝገባቸው የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ ከወጪ ቀሪያቸውን እንዳያሳዩ እና የበጀት አጠቃቀሙንም የተዛባ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.27.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት ለወጪው በጀት መያዙንና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ መመዝገባቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም አንድን ወጪ ሁለት ጊዜ መዝግቦ ሪፖርት ማቅረብ የመንግስት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ ከወጪ ቀሪያቸውን እንዳያሳዩ እና የበጀት አጠቃቀሙንም የተዛባ እንዲሆን ሊያደርግ እና ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡ ስለዚህ ወጪዎች ሁለት ጊዜ (በድጋሜ) እንዳይመዘገቡ ለሚመለከተው የስራ ክፍል በጥብቅ ማስመዝገብ ይኖረበታል፡፡ ለተጠቀሰውም ሂሳብ ማስተካከያ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

3.27.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

ማስተካከያ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

4. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

4.1.1 **ግኝት፣ በወቅቱ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣**

ዩኒቨርሲቲው ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ የሚወራረድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከሚታየው ውስጥ በድምሩ ብር 173,651,200.77 እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ መወራረድ ሲገባው ያልተወራረደ መሆኑ፣ዝርዝሩም

- በሂሳብ መደብ 4201 /ልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ/ ብር 859,952.54 ከ1 ወር- 3 ዓመት ለውሎ አበል ቅድሚያ የተከፈለ፣
- በሂሳብ መደብ 4202 ብር 16,687.39 የጥሬ ገንዘብ ጉድላትተ ለ3 ዓመት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4211 ብር 427,525.00 በተለለያዩ ጊዜ ለግዥ ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ ከ 1 ወር-1 ዓመት ያልተወራረደ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4253 /የዕቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ/ የሂሳብ መደብ የሚታየው ብር 170,557,299.54 ከ1 ወር- 3 ዓመት ያልተወራረደ መሆኑ፣

- በሂሳብ መደብ 4274 /ለሌሎች ቅድሚያ ክፍያ/ የሚታየው ብር 1,789,736.30 ከ1 ወር- 5 ዓመት ያልተወራረደ መሆኑ፣

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

4.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- የመንግስትን ገንዘብ በወቅቱ አለመሰብሰብ ለገንዘብ ጥፋትና ብክነት መንስዔ ሊሆን ይችላል፡፡
- በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረድ ቁጥጥር ካልተደረገ ለውዝፍ ሰነድ ክምችት መንስዔ ይሆናል፡፡
- ተሰብስቦ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ውስን ሀብት /ገንዘብ/ ያለሥራ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

4.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ውዝፍ የቅድሚያ ክፍያዎች በደንቡ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረዱ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ፣ የእርምት እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

4.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በአብዛኛዉ ክፍያ የተፈጸመባቸው ቅድመ ክፍያዎች የማጠናቀቅያ ጊዜያቸው ከሰኔ 30/10/2009 ዓ.ም በኂላ በመሆናቸው ስራውን ሰርተው ባለማጠናቀቃቸዉ ሲሆን የውል ጊዜያቸዉ ያለፈባቸዉ ነጋዴዎች /ግለሰቦች እና ድርጅቶች በህጋዊ መንገድ እንዲከፍሉ ጥብቅ ክትትል እየተደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

4.2.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ሚዛኑን ያልጠበቀ የተሰብሳቢ መክፍቻ ሂሳብ፣</u>

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/6 ፊደል መ መሠረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጊዜያዊ ሂሳቦች መዝጊያ ምዝገባ ተከናውኖ የዘመኑን ሂሳብ በመዝጋት ቋሚ ሂሳቦች ለቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፍ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበሩ ቋሚ ሂሳቦች በትክክለኛው የሂሳብ ሚዛን/Normal balance side/ ወደ ቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፋቸውን ኦዲት ሲደረግ፡

- በመክፍቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተሰብሳቢ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋት/ ሌጀሮች/ ብር 85,385,942.96 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን ክሬዲት ሂሳቡ የሚታይ መሆኑ፣

የመክፍቻ ሂሳብ/Opening balance/ በ Credit Balance የተያዘ ተሰብሳቢ ሂሳብ

Date	Opening balance	Account code	Subsidiary		Credit
01/11/2008	OB	4211	0001		192,148.58
01/11/2008	OB	4211	0002		166,278.68
01/11/2008	OB	4251			85,027,515.70
	Total				**85,385,942.96**

4.2.2 ስጋት፣

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውንና ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ካልተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርቶች የተቋሙን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በትክክል ላያሳዩ ይችላሉ፡፡

4.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ቋቶች ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይደረግ ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለሂሳቡ ተገቢውን ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል፡፡

4.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ከሐምሌ ሪፖርት የዞረ ባላንስ አለማሳየቱን በመግለጽ IBEX ድጋፍ ሰጪ ክፍል ባለሞያ በመጥራት የተስተካከለበትና የመ/ቤቱ ስህተት አለመሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ፣

5.1 ግኝት፣በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ፣

የዩኒቨርሲቲው ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ የሚከፈል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚታይ ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር **176,421.92** እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ መከፈል ሲገባው ሳይከፈል የተገኘ መሆኑ፣ዝርዝሩም

- በሂሳብ መደብ 5005 /ልዩልዩ የደመወዝ ተቀናናሽ/ ብር 165,515.46፣
- በሂሳብ መደብ 5027 /ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብቢር ሚ/ር/ ሌሎች ተከፋይ ብር 4,355.37፣
- በሂሳብ መደብ 5054 /ሌሎች የሂሳብ መያዣዎች/ በተለያዩ ጊዜያት የተያዘ ብር **6,551.09** ከወር-3 ዓመት ሳይከፈል የቆየ መሆኑን፤

5.2 ስጋት፣

ተከፋይ ሂሳቦችን ለባለቤቶቹ በወቅቱ አለመክፈል ለገንዘብ መጥፋት መንስኤ ሊሆን ይችላል።

5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ተከፋይ ሂሳቦችን ለባለቤቶቹ በወቅቱ መክፈል፤ የማይከፈሉ ከሆነም በፋይናንስ ህጉ መሰረት በሂሳቡ ላይ ተገቢው ውሳኔ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የደመወዝ ተቀናናሽ፣ ባለቤቱ ያልታወቀ እና ሌሎች የሂሳብ መያዣዎች ናቸው።

6. በጀት፣

6.1.1 ግኝት፣

ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደው በጀት በአግባቡ ስራ ላይ የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለመደበኛ(1800) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 14,698,892.48 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- ከውስጥ ገቢ(1900) ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 411,843.00 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤

- ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው ወጪ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 104,492,885.73 04 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

6.1.2 ስጋት፣

ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የታወጀለትን በጀት አለመጠቀሙ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም በላይ የሀገሪቱንም ውስን ሃብት ያለጥቅም እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው በተጨባጭ ሊሰራ ካቀደው ተግባር ጋር የበጀቱን አጠቃቀሙን በመገምገም የሚጠየቀው በጀት መረጃን መሠረት በማድረግ በበቂ ምክንያት በጥናት ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

6.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በሒሳብ መደብ 6313 ለዓመቱ ከተያዘ በጀት ውስጥ ብር 104,384,462.65 ለግዢ ኤጀንሲ በማዕቀፍ ለሚገዙ የመማር ማስተማር እዕቃዎች ለአቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ የተከፈል ሲሆን ይህም ክፍያ ዕቃዎቹን አቅራቢዎቹ ገቢ እስከሚያደርጉ ድረስ በወጪነት የማይመዘገቡ በመሆኑ በሥራ ላይ ያልዋለ በጀት የሚመስል እንጂ በሥራ ላይ ውሏል ብለዋል፣

6.2.1 ግኝት፣ በጀት ሳይያዝለት ለመሬት ካሣ የተከፈለ ክፍያ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 970/2008 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 24 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በሚለው ስር ‹‹የተፈቀደ በጀት መኖሩን ሳይረጋገጥ ከተፈቀደለት በጀት በላይ ወጪ ማድረግ ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል›› አዋጁ ቢያመለክትም፣ የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ በ30/01/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 149593 ብር 89,084.00 በግንባታ ምክንያት ከይዞታ ለሚነሱ አርሶ አደር ለአቶ ኤሊያስ አገኖ ኡጉሬ የተፈቀደ በጀት ሳይኖር በ6416 የሂሳብ መደብ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

6.2.2 ስጋት፣

የበጀት አጠቃቀም መመሪያው ተግባራዊ ባለመደረጉ ዩኒቨርሲቲው ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

6.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም በጀት በመንግሥት የበጀት አጠቃቀም መመሪያና ደንብ መሠረት እንዲከናወኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በ2008 ዓ.ም በፊት የካሳ ክፍያ ባለማለቁ ወደቀጣይ ዓመት ተላልፎ ክፍያዉ እንዲፈጽም በበላይ አመራር በመወሰኑና ግንባታ ለማካሄድ የካሳ ክፍያ ሳይፈፀም ግለሰቦቹ ቦታ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ ክፍያዉ የክልሉ መንግስት በአዋጁ መሰረት ባወጣው የካሳ ተመን መሰረት እንዲፈጸም ትዕዛዝ በመሰጠቱና የዕቅድ ክፍል በጀቱን ታሳቢ ባለማድረግ እና ባለመያዙ ዝዉዉር ተደረጎ ክፍያዉ እንዲፈጸም በመደረጉ መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

7. ንብረት፣

7.1 ግኝት፣ የንብረት አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ፣

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ ፣የመጠቀም ፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት የዩኒቨርስቲውን የንብረት አመዘጋገብ ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ በተደረገው ምልከታ፡-

- ብዛት ያላቸው አገልግሎት የማይሰጡ የውሀ ማጠራቀሚያ /ሮቶ/ በቤት ውስጥና ውጭ ላይ ተጠራቅመው የሚገኙ መሆኑ፣
- በተማሪዎች ምግብ ቤት አካባቢ የፍሳሽ ማስወገጃ የተበላሸ በመሆኑ ፍሳሽ በስርዓት የማይወገድ በመሆኑ በሰራተኞችና በተማሪዎች ጤና ላይ ችግር ሊፍጥር የሚችል መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

7.2 ስጋት፣

መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች በወቅቱ ካልተወገዱ የበለጠ በመበላሸት አካበቢውን ብክለት በማድረስ የሰራተኞችን ጤና ሊጎዱ ይችላሉ፡፡

7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- አገልግሎት የማይሰጡቱ ንብረቶች በማስወገድ ንጹህ የሥራ አካባቢን መፍጠር ይገባል፡፡
- የፍሳሽ ማስወገጃ በፍጥነት እንዲስተካከል ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

7.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- በምግብ ቤት አካባቢ የተበላሸው ፍሳሽን በአግባቡ ለማስወገድ ፍሳሽ ማስወገጃ ቦይ ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡
- አገልግሎት የማይሠጡ ሮቶዎችን ለማስወገድ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ቅድመ ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡

8. ልዩ ልዩ፣

8.1.1 ግኝት፣ የስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ፣

በዩኒቨርሲቲዉ የውስጥ ቁጥጥር ሰርዓት ሲታይ የፌደራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 13 እንደተመለከተው የመንግስት መ/ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የስጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው የሚገልጽ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲዉን በተመለከተ የስጋት ምንጮች ዳሰሳ ያልተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

8.1.2 ስጋት፣

በዩኒቨርሲቲዉ የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ አለመኖሩ በሃብት ና በንብረት አስተዳደር ላይ የላላ የውስጥ ቁጥጥር ሰርዓት ሊያስከትል ይችላል፡፡

8.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

በዩኒቨርሲቲዉ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች ለይቶ ለማወቅና እንዲቀረፍም ብሎም ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ዩኒቨርሲቲዉ የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

8.1.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

ጥናት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

8.2.1 **ግኝት፣ በቅጥርና በዕድገት ያልተሞሉ ክፍት የሥራ መደቦች፣**

ዩኒቨርሲቲዉ በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት በአግባቡ ለመፈጸም ይችል ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በሰው ኃይል መሙላት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ነገር ግን ዩኒቨርሲቲው ከተፈቀደለት 1299 የሥራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 638 ሲሆን 661 (51%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

8.2.2 **ስጋት**

የተሟላ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት ዩኒቨርሲቲዉ ዕቅዱን እንዳያሳካ ምክንያት ሊሆን እንዲሁም በአሰራር ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

8.2.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ለዩኒቨርሲቲዉ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሞሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

8.2.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

በቀረበዉ የማሻሻያ እረምጃ ሀሳብ መሰረት ዩኒቨርሲቲዉ ሀላፊነቱን ለማወጣት በእንዲሁም ራእይ ተልኮ ለማሳካት የሰዉ ሀይል መሰረታዊ ሚና አለዉ፡፡ በመሆኑም በ2009 ዓም በዘርፉ በርካታ በለሞያዎች እና ሰራተኞችን በከፍተኛ ሁኔታ እያሟላን የምንገኝ ሲሆን በግኝቱ የማሻሻያ እረምጃ መሰረት የምንፈጽም መሆኑን እንገልጻለን ብለዋል፡፡

የተወሰደ እርምጃ/ ማስተካከያ

- የመጀመሪያው ማስተካከያ ከላይ እንደተገለጸው በከፍተኛ ሁኔታ በሥራ አስፈላጊነት የሰው ኃይል የማሟላት ሥራ እየተሠራ በአሁን ወቅት 725 የሚደርስ የአስተዳደር

ሠራተኛ ያለን ሲሆን በተፈቀደልን መዋቅር ልክ ማሟላት ያልተቻለው በመዋቅሩ አብዛኛውን መደብ ይዞ ያለው የተማሪዎች ምግብ ቤት እና የጽዳት ሥራ መደብ ሲሆን በእነዚህ መደቦች ሁሉ የተሟላ ሰው ቢቀጠር የዩኒቨርሲቲውን ፍልጎት የማያሟላ በመሆኑ በመደቦቹ ላይ ቋሚ ቅጥር እየፈጸምን ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው እነዚህን ሥራዎች አውትሶርስ በማድረግ በማህበራት እያሰራ በመሆኑ የታየ ክፍተት ነው፡፡

- ሁለተኛው ማስተካከያ ዩኒቨርሲቲ በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት ለመፈጸም የሰው ኃይል መሠረታዊ ሚና እንዳለው ታምኖ በመዋቅሩ በተፈቀዱ መደቦች ሰው አሟልተን በቂ ባለመሆናቸው ተጨማሪ መደቦች እንድፈቀዱልን ጠይቀን ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር 155 ተጨማሪ መደቦችን የፈቀደበት በማስረጃነት አቅርበናል፡፡ ይህም ዩኒቨርሲቲው ተልዕኮውን ለመወጣት በመዋቅሩ ብቻ ሳይገደብ አስፈላጊውን የሰው ኃይል እያሟላ እንዳለ ማሳያ ነው፡፡

8.3.1 ግኝት፣ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ላይ እርምጃ አወሳሰድ፣

1. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰርት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፈዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡ በዚሁ መሰረት ዩኒቨርሲተውን በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

    - ዩኒቨርሲቲው በ2008 በጀት ዓመት ከልዩ ልዩ የውስጥ ገቢ ምንጮች የሚሰበስበውን በየሂሳብ ርዕሶቹ የሚመዘገብ ቢሆንም፣ በዝርዝር ሂሳብ መመዝገቢያ(TR) መሠረት ተመዝግቦ የተገኘው ብር 21,500,537.27 ሲሆን፣

በሂሳብ ቋት የተመዘገበው ደግሞ ብር 14,377,771.31 በመሆኑ በልዩነት ብር 7,122,765.96 የሚታይ መሆኑን፣ ዓመታዊ ሪፖርት የማይዘጋጅና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት የማይደረግ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ ‹‹ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ መጠን ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከ አሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ መጠን እና ጥቅማ ጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ሲል በጥብቅ እንዳሳሰበ ›› መመሪያው ቢያመለክትም፣ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ መጠን ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-
    - ለ14 ሠራተኞች ከብር 1,500-20,000.00 በሥራ አመራሩ ውሳኔ የማበረታቻ ሽልማት ለቢ.ኤስ.ሲ ዕቅድ የሠሩ በሚል ብር 68,000.00 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
    - ዩኒቨርስቲው ሠራተኞች ሥራ ላይ ስለመሆናቸው ሳያረጋግጥ በድምሩ ብር 42,945.08 ሰራተኞቹ ዩኒቨርሲቲውን ከለቀቁ በኋላ ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር ደመወዝ በሰራተኞች የግል የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑን፤
    - ዩኒቨርሲቲው ለለማ ኢንተርናሽናል ሆቴል ብር 40,026.55 መክፈል ሲገባው፣ ብር 10,213.53 በብልጫ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱ፤

2. ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ድርጅቶች ግዥ ሲፈጽም ብር 52,250.38 የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ብር 8,111.77 የተቀናሽ ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 60,362.15 ከአቅራቢው ሳይቀነስ በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱና ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፤

8.3.2 ስጋት፤

በኦዲት ሪፖርቱ ላይ እርምጃ ባለመወሰዱ ምክንያት ኦዲተሩ የውስጥ ቁጥጥሩና የአሰራር ስርዓቱ ላይ አሜኔታ እንዳይኖረውና ለተጨማሪ ብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

8.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፍ ብሎም ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በኦዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት በአስቸኳይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል፡፡

8.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፤

አብዛኞቹ ማስተካከያ እየተደረገ ይሲሆን ቀሪዎችም የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!